# የዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ የ2006 የስራ ዘመን አመታዊ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት

**ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ**
**ሐምሌ 2006**
**ዓዲግራት**

**ይዘት** **ገፅ**


| | | |
|---|---|---|
| 1 | መግቢያ | 3 |
| 2 | መሰረታዊ አሃዛዊ መረጃ | 3 |
| | 2.1. ነባርና አዲስ ተማሪዎች | 3 |
| | 2.2. የአካዳሚክ ሰራተኞች | 10 |
| | 2.3. ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች | 14 |
| 3 | የተመደበልን ባጀትና አጠቃቀሙ | 16 |
| | 3.1. መደበኛ ባጀት | 16 |
| | 3.2. ካፒታል ባጀት | 17 |
| | 3.3. የግንባታ ስራዎች አፈፃፀም | 18 |
| 4 | የእቅድ አፈፃፀም | 20 |
| | 4.1. መማር ማስተማር | 20 |
| | 4.2. ምርምርና ህብረተሰብ አገልግሎት | 22 |
| | 4.3. ለሴት ተማሪዎች የተደረገ ድጋፍ | 26 |
| | 4.4. የዩኒቨርሲቲው የመጀመርያ ተማሪዎች ምረቃ | 27 |
| | 4.5. የ2006 አመታዊ የስራ አፈፃፀም ሰንጠረዥ | 28 |
| 5 | ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች | 51 |
| 6 | ለ2007 የትምህርት አመት እቅድ መነሻ ነጥቦች | 53 |
| 7 | ተጨማሪ ማብራርያዎች (Appendix) | 55 |

## 1. መግቢያ

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ 2004 ስራቸውን ከጀመሩት አዳዲስ ዩኒቨርሲቲው አንዱ ሲሆን ተማሪን የመቀበል አቅሙን በፍጥነት በማሳደግ በ2006 የትምህርት አመት ከአራት ሺ በላየ አዲስ ተማሪዎችን በመቀበል ሁለተኛ አመቱን በሚያከብርበት ጊዜ የመደበኛ ተማሪዎች ቁጥር 7291 የደረሰ ሲሆን ጠቅላላ የተማሪዎቹ ቁጥር (የማታ እና የክረምት ተከታታይ ተማሪዎችን ጨምሮ 8378 ደርሷል። ዩኒቨርሲቲው ግንቦት 18/2003 ዓም በወጣው ነጋሪት ጋዜጣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 223/2003 **"ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ"** በሚል የተቋቋመ መንግስታዊ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ሲሆን ተጠሪነቱም ለትምህርት ሚኒስቴር ነው።

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ እንደሌሎች የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ሶስት ዋና ዋና ተልእኮዎች ያሉት ሲሆን እነሱም፤ ማስተማር፤ ምርምር እና የህብረተሰብ አገልግሎት ስራዎችን ማከናወን ናቸው። ዩኒቨርሲቲያችን እነዚህን ተልእኮዎች በኣጥጋቢ መልኩ ለማሳካት ተገቢውን ዝግጅት በማድረግ የ2006 ዓመታዊ እቅዱን ካዘጋጀ በኋላ ከዝግጅት ምእራፍ ወደ ትግበራ ምእራፍ ተሸጋግሮ በእቅዱ መሰረት ተግባራቱን ያከናወነ ሲሆን በማጠቃለያ ምእራፍ ላይም የአመቱን የስራ አፈፃፀም ግምገማ በየደረጃው ያደረገ ሲሆን የአፈፃፀም ሪፖርቱ እነሆ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## 2. መሰረታዊ አሃዛዊ መረጃ

### 2.1 ነባር እና አዲስ ተማሪዎች

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ በ2004 የመጀመርያ ተማሪዎችን በመቀበል ትምህርት ሲጀምር የተመደቡለት ተማሪዎች 960 ነበር። እነዚህ ተማሪዎች በአራት ኮሌጆችና በአስራ ሶስት የትምህርት ክፍሎች እንዲመደቡ ተደርጓል። በ2005 ለሁለተኛ ጊዜ ተማሪዎችን ስንቀበል የተመደቡልን መደበኛ ተማሪዎች ብዛት 3141 ተማሪዎች እና 117 ኤርትራውያን ስደተኞች በድምሩ 3258 ተማሪዎች በስድስት ኮሌጆች እና በ26 የትምህርት ፕሮግራሞች ተመድበው እንዲማሩ ተደርጓል። በ2006 የተመደቡት ተማሪዎች በመደበኛነት 4289 እና የኤርትራ ስደተኞች 130 በድምሩ 4419 ተማሪወች ናቸው። እነዚህ ተማሪዎች በስድስት ኮሌጆችና በ31 የትምህርት ክፍሎች (የትምህርት ፕሮግራሞች) እንዲመደቡ ተደርገው ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። በ2005 መገባደጃ ላይ ለ2006 የምንቀበላቸው ተማሪዎች እንድናሳውቅ በቀረበልን ጥያቄ መሰረት 4460 ያህል አዲስ ተማሪዎችን መቀበል እንደምንችል አሳውቀን የነበረ ሲሆን ይሄን ያህል ተማሪዎችን ለመቀበል እንችላለን ብለን እቅድ የያዝንበት ምክንያት የሁለተኛው ዙር የግንባታ ስራዎች (54 ዋና ዋና ብሎኮችን የያዘው) ለ2006 ይደርሳሉ የሚል እሳቤ በማድረግ እና ከግንባታው ስራ ጎን ለጎን ደግሞ የመምህራንና እና የሰራተኞች ቅጥር እና ዝውውር እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ ማቴርያሎች (እንደነ አልጋ ወንበር ወዘተ) በወቅቱ አቅርቦታቸውን ማጠናቀቅ እንችላለን የሚል ዝግጅት እና እንቅስቃሴ በማድረግ ነበር። በዚሁም መሰረት ግንባታው ከሞላ ጎደል የተጠናቀቀ በመሆኑ እና ሌሎች ዝጅግቶችም በተጓዳኝ ስለተደረጉ የተጠቀሰውን ያህል የተማሪዎች ቁጥር ካለብዙ ችግር ለመቀበል አስችሎናል። በ2006 የትምህርት ዘመን አዲስ የተጨመሩ የትምህርት መስኮች 1)በኢንጂነሪንግ ኮሌጅ፤ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ 2) በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ፤ ማርኬቲንግ 3) በማህበራዊ ሳይንስ ኮሌጅ፤ ሶስዮሎጂ እና ህግ ናቸው። በድምሩ በአመቱ የተጨመሩት የትምህርት መስኮች ወይም ትምህርት ክፍሎች አራት ናቸው።

በሚቀጥለው ሰንጠረዥ (ሰንጠረዥ 1) እንደተመለከተው የመሰናዶ ትምህርት በማጠናቀቅ እና የዩኒቨርሲቲ የመግብያ ፈተና በማለፍ ወደ ዓዲግራት ዩኒቨርሰቲ የተመደቡ መደበኛ ተማሪዎች (ማለትም የኤርትራ ስደተኞችን ሳይጨምር) ብዛት 4289 ሲሆን በየትምህርት ዘርፉ በፆታ ስብጥራቸው የሚከተለውን ይመስላል። በዚሁም መሰረት አብዛኛዎቹ በኢንጂነሪንግ ሳይንስ መስክ የተመደቡልን ሲሆን የሴቶች ብዛት ደግሞ 39.6% ነው።

ሰንጠረዥ 1. ለ2006 የተመደቡልን አዲስ መደበኛ ተማሪዎች በትምህርት ዘርፍና በፆታ

| Field of Study | M | F | T | % share | % of Female |
|---|---|---|---|---|---|
| Engineering Sciences | 1242 | 500 | 1742 | 40.62 | 28.70 |
| Computer Science | 83 | 57 | 140 | 3.26 | 40.71 |
| Natural and Computational Sc | 153 | 502 | 655 | 15.27 | 76.64 |
| Medicine | 85 | 34 | 119 | 2.77 | 28.57 |
| Public Health Officer | 45 | 15 | 60 | 1.40 | 25.00 |
| Other Health Sciences | 77 | 43 | 120 | 2.80 | 35.83 |
| Agricultural and Natural Resouce | 104 | 76 | 180 | 4.20 | 42.22 |
| Business and Economics | 545 | 256 | 801 | 18.68 | 31.96 |
| Law | 49 | 11 | 60 | 1.40 | 18.33 |
| Other Social Sciences and Humanities | 206 | 206 | 412 | 9.61 | 50.00 |
| Total | 2589 | 1700 | 4289 | 100.00 | 39.64 |
| Percentage Share | 60.36 | 39.64 | 100.00 | | |

**በሰንጠረዥ 2 እንደተቀመጠው ወደ ዩኒቨርሲቲው የተመደቡ ተማሪዎች ከሁሉም ክልል የተመደቡ ሲሆን አብዛኛዎቹ ተማሪዎች (ማለትም 53.6%) ከትግራይ ክልል የተመደቡ ናቸው። ከትግራይ ቀጥሎ በተማሪዎች ብዛት በቅደም ተከተላቸው ከአማራ (14%) ከኦሮሚያ (10.5%) ከአዲስ አበባ (10.3%) እና ከደቡብ ህዝቦች (7.4%) የተመደቡት ይገኙበታል።**

ሰንጠረዥ 2. ለ2006 የተመደቡልን አዲስ መደበኛ ተማሪዎች በመጡበት ክልል

| **ክልል/ከተማ** | **Engin.** | **Comp.** | **NCS** | **MD** | **PHO** | **OHS** | **Agric** | **BE** | **Law** | **OSSH** | **Total** | **Percent** |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ትግራይ** | 1180 | 91 | 396 | 24 | 24 | 80 | 137 | 179 | 25 | 164 | 2300 | **53.63** |
| **አማራ** | 165 | 23 | 58 | 26 | 12 | 16 | 19 | 202 | 7 | 73 | 601 | **14.01** |
| **ኦሮሚያ** | 101 | 6 | 48 | 15 | 8 | 10 | 8 | 186 | 10 | 58 | 450 | **10.49** |
| **ደቡብ ህዝቦች** | 60 | 6 | 17 | 12 | 6 | 3 | 7 | 146 | 10 | 51 | 318 | **7.41** |
| **አዲስ አበባ** | 205 | 10 | 66 | 41 | 9 | 9 | 3 | 58 | 5 | 34 | 440 | **10.26** |
| **ሶማሊ** | 5 | | 34 | | | 1 | 1 | 16 | 2 | 10 | 69 | **1.61** |
| **ዓፋር** | 2 | | 6 | | | | 3 | 2 | | 2 | 15 | **0.35** |
| **ጋምቤላ** | 1 | 1 | 4 | | | | | 4 | | 4 | 14 | **0.33** |
| **ሃረሪ** | 3 | | 1 | 1 | | | | 2 | | | 7 | **0.16** |
| **ድሬዳዋ** | 4 | 1 | 3 | | 1 | | 1 | 2 | | 2 | 14 | **0.33** |
| **ቤንሻንጉል ጉምዝ** | 15 | 2 | 22 | | | | 1 | 4 | 1 | 14 | 59 | **1.38** |
| **ሌሎች አገሮች** | 1 | | | | | 1 | | | | | 2 | **0.05** |
| **ድምር** | **1742** | **140** | **655** | **119** | **60** | **120** | **180** | **801** | **60** | **412** | **4289** | **100** |

**የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ውጤታቸውን በተመለከተ ደግሞ ውጤቱ የሚታረመው ከ700 ሲሆን በየተመደቡበት የትምህርት ዘርፍ ያገኙት የመግቢያ ፈተና ውጤት በዝቅተኛ ደረጃ ሊቀመጥ የሚችል ነው። በሚቀጥለው ሰንጠረዥ እንደሚታየው አብዛኛዎቹ (ማለትም 58%) የተመደቡልን ተማሪዎች ያገኙት ውጤት ከ300 እስከ 350 ያለውን ነው። በማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ ከተመደቡልን ተማሪዎች ውስጥ 85% የሚሆኑት ያገኙት የመግቢያ ፈተና ውጤት ከ300 በታች**

ነው። ከተመደቡልን ተማሪዎች ውስጥ ከ500 በላይ ውጤት ያገኘ አንድም ተማሪ ያልተመደበ ሲሆን የተሻለ ውጤት ያላቸው ሊባሉ የሚችሉት (ማለትም ከ450 እስከ 500 ያገኙ) በህክምና እና በጤና ረዳት የተመደቡት ናቸው። በአጠቃላይ የተማሪዎች ምደባ የሚያሳየው ወደ ዩኒቨርሲቲው የሚመደቡ ተማሪዎች በተነፃፃሪ ዝቅተኛ ነጥብ ያላቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው። ሆኖም የመግቢያ ውጤት ብቻ በማየት ተማሪዎቹ በጥቅሉ ብቃታቸው አነስተኛ ነው ለማለት የማያስደፍር ሲሆን ዩኒቨርሲቲ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ጠንክሮ ከተሰራበት (በዩኒቨርሲቲውም በተማሪዎችም) ብቃታቸው ወደተፈለገበት ደረጃ ማድረስ የማይቻልበት ምክንያት ሊኖር አይችልም። በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች ወደዩኒቨርሲቲዎች የሚመደቡት በሚያመለክቱት ምርጫ መሰረት ስለሆነ ዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ ነጥብ የሚያገኙ ተማሪዎች እንዲመርጡት (ተመራጭ እንዲሆን) ጠንክሮ መስራት እንዳሚገባው መገንዘብ ይቻላል።

ሰንጠረዥ 3. የተመደቡልን ተማሪዎች ባገኙት የፈተና ውጤት

| Field of Study | >=500 | [450, 500) | [400, 450) | [350, 400) | [300, 350) | <300 | Total |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| Engineering Sciences | | 3 | 45 | 706 | 988 | | 1742 |
| Computer Science | | | 9 | 131 | | | 140 |
| Natural and Computational Sc | | | 5 | 30 | 620 | | 655 |
| Medicine | | 119 | | | | | 119 |
| Public Health Officer | | 60 | | | | | 60 |
| Other Health Sciences | | 2 | 118 | | | | 120 |
| Agricultural and Natural Resouce | | | 20 | 97 | 63 | | 180 |
| Business and Economics | | 1 | 7 | 23 | 770 | | 801 |
| Law | | 1 | 3 | 56 | | | 60 |
| Other Social Sciences and Humanities | | | 2 | 1 | 58 | 351 | 412 |
| Total | 0 | 186 | 209 | 1044 | 2499 | 351 | 4289 |
| Percentage Share | 0.00 | 4.34 | 4.87 | 24.34 | 58.27 | 8.18 | 100.00 |

ከላይ በየሰንጠረዡ ከተቀመጠው የአዲስ መደበኛ ተማሪዎች በተጨማሪ 130 ኤርትራውያን ተማሪዎች የተመደቡልን ሲሆን አመዳደባቸውም 92 (ከነዚህ ውስጥ 1 ተማሪ ሴት ናት) ተማሪዎች በተፈጥሮ ሳይንስ እና 38 ደግሞ (ከነዚህ ውስጥ 1 ሴት ተማሪ ናት) በማህበራዊ ሳይንስ ነው። ስለዚህ ከላይ እንደተቀመጠው በ2006 የተመደቡልን ጠቅላላ የተማሪዎች ብዛት 4419 ሲሆን ከነዚህም ውስጥ የሴት ተማዎች ብዛት 1702 (ወይም 38.5%) ነው።

ኢ.ዲስ ተማሪዎችን ከተቀበልን በኋላ የትምህርት ክፍል መረጣና ምደባ የተደረገ ሲሆን ምደባው ተደርጎ በአንደኛ ሰሚስተር ተመዝግበው ትምህርት የጀመሩ የመደበኛ ተማሪዎች ብዛት (የአንደኛ አመት፤ የሁለተኛ አመት እና የሶስተኛ አመት መደበኛ ተማሪዎች) 7291 ነው። በአንደኛ ሰሚስተር ከተመዘገቡት የመደበኛ ተማሪዎች ቁጥር ውስጥ 4519 (ወይም 62%) ወንዶች የነበሩ ሲሆኑ የተቀሩት 2772 ተማሪዎች (ወይም 38%) ደግሞ ሴቶች ነበሩ። ወደ ዩኒቨርሲቲው ከተመደቡት 4419 አዲስ ተማሪዎች ውስጥ በአንደኛ ሰሚስተር ተመዝግበው ትምህርት የጀመሩት 4289 (97%) ሲሆኑ የተቀሩት ተማሪዎች ግን ሪፖርት አላደረጉም። በአንደኛ አመት ከተመዘገቡት ተማሪዎች ውስጥ በ2005 በትምህርት ድክመት ምክንያት ከአንደኛ አመት ጋር ተመዝግበው ትምህርት እንዲቀጥሉ የተገደዱትም የሚገኙበት መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል። የተወሰኑ ተማሪዎች ደግሞ ከኛ ወደ ሌላ ዩኒቨርሲቲ የተዛወሩ እንዲሁም ከሌላ ዩኒቨርሲቲ በዝውውር የተቀበልናቸው እንዳሉም የሚታወቅ ነው።

በሁለተኛው ሰሚስተር ተመዝገበው ትምህርት የተከታተሉት መደበኛ ተማሪዎች ብዛት 6816 ነው። አንደኛ ሰሚስተር ላይ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ከነበሩት 7291 ተማሪዎች ውስጥ በሁለተኛው ሰሚስተር ላይ በተለያየ ምክንያት ትምህርት ያቋረጡ ተማሪዎች ስለነበሩ እና በሌላ

በኩል ደግሞ በዳግመ ቅበላ (readmission) በሁለተኛ ሰሚስተር የገቡ ተማሪዎችም መኖራቸው ታሳቢ በማድረግ 6816 ተማሪዎች በሁለተኛው ሰሚስተር ተመዝግበው ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። ከነዚህ ውስጥ የሴቶች ቁጥር 2488 (ወይም 36.5%) ነው። በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መሰረት በእቅዱ ዘመን መጨረሻ ላይ የዩኒቨርሲቲ ሴት ተማሪዎች ቁጥር የጠቅላላ ተማሪዎች 40% ለማድረስ የሚል ሲሆን በዩኒቨርሲቲያችን ያለው የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከዚህ ታርጌት ጋር ተቀራራቢ መሆኑ ያሳያል። በ2006 በሁለተኛ ሰሚስተር የተመዘገቡ ተማሪዎች ዝርዝር በሰንጠረዥ 4 የተቀመጠውን ይመስላል።

በአንደኛ ሰሚስተር ከነበሩን ተማሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ትምህርት ያቋረጡ ተማሪዎች ቁጥር 522 ሲሆን ዝርዝሩ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተጠቃሎ ቀርቧል።

| አይነት | አንድኛ አመት | | | ሁለተኛ አመት | | | ሶስተኛ አመት | | | ጠቅላላ ድምር | | | ፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | |
| ተፈቅዶላቸው ያቋረጡ (Withdrawals) | 54 | 21 | 75 | 13 | 5 | 18 | 2 | 2 | 4 | 69 | 28 | 97 | **1.33** |
| ሳያስፈቅዱ ያቋረጡ (Dropouts) | 96 | 107 | 203 | 22 | 18 | 40 | | 1 | 1 | 118 | 126 | 244 | **3.34** |
| በትምህርት ድክመት (Dismissals) | 47 | 71 | 118 | 20 | 18 | 38 | 2 | 23 | 25 | 69 | 112 | 181 | **2.48** |
| ድምር | 197 | 199 | 396 | 55 | 41 | 96 | 4 | 26 | 30 | 256 | 266 | 522 | **7.16** |

ትምህርት ካቋረጡት ተማሪዎች ውስጥ አብዛኞዎቹ (ማለትም 3.34%) በራሳቸው ፈቃድ እና ዩኒቨርሲቲውን ሳያሳውቁ ያቋረጡ (drop outs) ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ (ማለትም 2.48%) በትምህርት ድክመት መቀጠል ያልቻሉት ናቸው። በትምህርት ድክመት ትምህርት ካቋረጡት ውስጥ አብዛኞዎቹ (ማለትም 62%) ሴቶች ናቸው። በአንድ በኩል በዩኒቨርሲቲው ያሉት የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከወንድ ተማሪዎች ያነሰ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በትምህርት ድክመት ምክንያት ትምህርት መቀጠል ያልቻሉት አብዛኞዎቹ ሴት ተማሪዎች መሆናቸው በተለይ ሴት ተማሪዎችን መሰረት ያደረጉ የድጋፍ ስራዎች በስፋት መሰራት እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው። በራሳቸው ፈቃድ ትምህርት ያቋረጡ ተማሪዎች ያቋረጡበት ምክንያት የተለያየ ሊሆን እንደሚችል የሚገመት ሲሆን ከምክንያቶቹ በዋናነት ሊጠቀሱ የሚችሉት ትምህርቱን አንችለውም የሚል ስጋት፤ ከቤተሰብ ተለይቶ ለመኖር መቸገር፤ ከህመም ጋር የተያያዙ ችግሮች፤ እና የኢኮኖሚ ችግር እንደሆኑ ይገመታል። በድምሩ በአንደኛ ሰሚስተር ተመዝግበው ትምህርት ከጀመሩት ውስጥ 7.16% (ወይም 522 ተማሪዎች) በሁለተኛ ሰሚስተር መቀጠል አልቻሉም። በተለያየ ምክንያት ትምህርት ያቋረጡ ተማሪዎች ቁጥር በርካታ ስለሆነ ማቋረጥን መቀነስ የሚያስችሉ የተለያዩ ዘዴዎችን ዩኒቨርሲቲው መጠቀም እንዳለበት የሚያስገነዝብ ነው።

ሰንጠረዥ 4. በ2006 በየኮሌጅና ትምህርት ክፍሉ በሁለተኛ ሰሚስተር የተመዘገቡ መደበኛ ተማሪዎች

| College | Department/Program | year I | | | year II | | | year III | | | Total | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | M | F | T | M | F | T | M | F | T | M | F | T |
| Engineering and Technology | Civil Engineering | 462 | 234 | 696 | 270 | 122 | 392 | 57 | 78 | 135 | 789 | 434 | 1223 |
| | Electrical and Engineering | 215 | 80 | 295 | 132 | 27 | 159 | 29 | 21 | 50 | 376 | 128 | 504 |
| | Chemical Engineering | 132 | 60 | 192 | 82 | 26 | 108 | 22 | 24 | 46 | 236 | 110 | 346 |
| | Construction Technology and Mgt. | 117 | 64 | 181 | 78 | 28 | 106 | | | 0 | 195 | 92 | 287 |
| | Mechanical Engineering | 310 | 48 | 358 | 159 | 19 | 178 | 34 | 11 | 45 | 503 | 78 | 581 |
| | Information Technology | 26 | 29 | 55 | | | 0 | | | 0 | 26 | 29 | 55 |
| | Computer Science | 55 | 37 | 92 | 21 | 15 | 36 | | | 0 | 76 | 52 | 128 |
| | sub total | 1317 | 552 | 1869 | 742 | 237 | 979 | 142 | 134 | 276 | 2201 | 923 | 3124 |
| Natural and computational science | Biology | 37 | 103 | 140 | 40 | 52 | 92 | 8 | 42 | 50 | 85 | 197 | 282 |
| | Chemistry | 22 | 63 | 85 | 30 | 37 | 67 | 7 | 54 | 61 | 59 | 154 | 213 |
| | Mathematics | 21 | 43 | 64 | 29 | 11 | 40 | 10 | 22 | 32 | 60 | 76 | 136 |
| | Statistics | 21 | 27 | 48 | 33 | 8 | 41 | | | 0 | 54 | 35 | 89 |
| | Physics | 20 | 39 | 59 | 33 | 13 | 46 | 4 | 15 | 19 | 57 | 67 | 124 |
| | Geology | 24 | 27 | 51 | 24 | 10 | 34 | | | 0 | 48 | 37 | 85 |
| | Sport Science | 16 | 40 | 56 | 25 | 17 | 42 | | | 0 | 41 | 57 | 98 |
| | sub total | 161 | 342 | 503 | 214 | 148 | 362 | 29 | 133 | 162 | 404 | 623 | 1027 |
| Business and Economiccs | Economics | 152 | 9 | 161 | 97 | 9 | 106 | 24 | 14 | 38 | 273 | 32 | 305 |
| | Accounting and Finance | 168 | 104 | 272 | 122 | 60 | 182 | 22 | 38 | 60 | 312 | 202 | 514 |
| | Marketing | 37 | 21 | 58 | | | | | | | 37 | 21 | 58 |
| | Management | 142 | 83 | 225 | 92 | 63 | 155 | 25 | 28 | 53 | 259 | 174 | 433 |
| | sub total | 499 | 217 | 716 | 311 | 132 | 443 | 71 | 80 | 151 | 881 | 429 | 1310 |
| Social science and humanities | English Languade and Literature | 15 | 23 | 38 | 26 | 20 | 46 | 7 | 13 | 20 | 48 | 56 | 104 |
| | Civics and Ethical Studies | 48 | 32 | 80 | 28 | 16 | 44 | 17 | 19 | 36 | 93 | 67 | 160 |
| | Psychology | 34 | 17 | 51 | 32 | 25 | 57 | | | 0 | 66 | 42 | 108 |
| | Law | 44 | 9 | 53 | | | | | | | 44 | 9 | 53 |
| | Sociology | 57 | 58 | 115 | | | | | | | 57 | 58 | 115 |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Geography and Environmental Science | 36 | 41 | 77 | 26 | 29 | 55 | | | 0 | 62 | 70 | 132 |
| | sub total | 234 | 180 | 414 | 112 | 90 | 202 | 24 | 32 | 56 | 370 | 302 | 672 |
| Agriculture and Environmental Science | Plant Science, Crop production | 36 | 23 | 59 | 19 | 12 | 31 | | | 0 | 55 | 35 | 90 |
| | Animal and wild life Science,Animal Production | 49 | 9 | 58 | 27 | 2 | 29 | | | 0 | 76 | 11 | 87 |
| | Natural resource management | 20 | 25 | 45 | 17 | 19 | 36 | | | 0 | 37 | 44 | 81 |
| | sub total | 105 | 57 | 162 | 63 | 33 | 96 | 0 | 0 | 0 | 168 | 90 | 258 |
| Medicine and Health Science | Medicine | 82 | 27 | 109 | 35 | 11 | 46 | | | 0 | 117 | 38 | 155 |
| | Nursing | 36 | 20 | 56 | 16 | 14 | 30 | | | 0 | 52 | 34 | 86 |
| | Midwifery | 39 | 21 | 60 | 22 | 4 | 26 | | | 0 | 61 | 25 | 86 |
| | Health Officer | 44 | 14 | 58 | 30 | 10 | 40 | | | 0 | 74 | 24 | 98 |
| | sub total | 201 | 82 | 283 | 103 | 39 | 142 | 0 | 0 | 0 | 304 | 121 | 425 |
| Over total | | 2517 | 1430 | 3947 | 1545 | 679 | 2224 | 266 | 379 | 645 | 4328 | 2488 | 6816 |

የፆታ ሰብጥርን በተመለከተ ከአጠቃላይ መደበኛ ተማሪዎች 4328 (ወይም 63.5%) ወንዶች ሲሆኑ የተቀሩት 2488 ተማሪዎች (ወይም 36.5%) ደግሞ ሴቶች ናቸው። የ70፤ 30 ስርጭት በተመለከተ ደግሞ በየባንዱ የሚከተለውን ይመስላል።

ሰንጠረዥ 5. የ70፤30 ስርጭት (መደበኛ ተማሪዎች)

| ባንድ | ወ | ሴ | ድ | ፐርሰንት | 70፡30 ቀመር |
|---|---|---|---|---|---|
| ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ (ባንድ 1) | 2201 | 923 | 3124 | 0.46 | |
| ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ (ባንድ 2) | 404 | 623 | 1027 | 0.15 | |
| ህክምናና ጤና ሳይንስ (ባንድ 3) | 304 | 121 | 425 | 0.06 | |
| ግብርና (ባንድ 3) | 168 | 90 | 258 | 0.04 | 0.71 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ (ባንድ 5) | 881 | 429 | 1310 | 0.19 | |
| ህብረተሰብ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ (ባንድ 6) | 370 | 302 | 672 | 0.1 | 0.29 |
| ድምር | 4328 | 2488 | 6816 | 1 | |
| ፐርሰንት | 0.635 | 0.365 | 1 | | |

ከላይ በሰንጠረዥ 5 እንደተቀመጠው በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲሟላ የሚፈለገው ከተማሪዎቹ 70% በተፈጥሮ ሳይንስ መስኮች (ባንድ 1፣ 2፣ 3 እና 4) ሲሆን የተቀሩት 30% ደግሞ በማህበራዎ ሳይንስ መስኮች (ማለትም ባንድ 5 እና 6) ነው። በዩኒቨርሲቲያችን ያለው የመደበኛ ተማሪዎች ስብጥር 71% ያህሉ በተፈጥሮ ሳይንስ እና 29% ያህሉ ደግሞ በማህበራዎ ሳይንስ በሚገኙ ትምህርት ክፍሎች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ። በተፈጥሮ ሳይንስ መስኮች ያሉት ተማሪዎች ብዛት በአገር አቀፍ ከሚፈለገው ቀመር በተመሳሳይ ደረጃ ያለ መሆኑን ከሰንጠረዡ መረዳት ይቻላል።

ዩኒቨርሲቲው ከመደበኛ ተማሪዎች በተጨማሪ የማታ ተከታታይ ትምህርተ ተማሪዎች እና የክረምት ተከታታይ ትምህርት ተማሪዎች ያሉት ሲሆን በተከታታይ ትምህርት ትምህርታቸውን የተከታተሉት ተማሪዎች ብዛት በሚከተሉት ሁለት ሰንጠረገኙች የተቀመጠውን ይመስላል፤

ሰንጠረዥ 6፡ የማታ ተከታታይ ትምህርት ተማሪዎች

| | | Year I | | | Year II | | | Total | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| College | department | M | F | T | M | F | T | M | F | T |
| Engineering and technology | Civil Engineering | 83 | 8 | 91 | 68 | 8 | 76 | 151 | 16 | 167 |
| | Electrical and Engineering | | | | 15 | 1 | 16 | 15 | 1 | 16 |
| | construction and technology Mgt. | 36 | 5 | 41 | | | | 36 | 5 | 41 |
| | Information Technology | 11 | 29 | 40 | | | | 11 | 29 | 40 |
| | sub total | 130 | 42 | 172 | 83 | 9 | 92 | 213 | 51 | 264 |
| Buisnss and economics | Accounting and Finance | 102 | 84 | 186 | | | | 102 | 84 | 186 |
| | Management | 26 | 19 | 45 | 17 | 17 | 34 | 43 | 36 | 79 |
| | sub total | 128 | 103 | 231 | 17 | 17 | 34 | 145 | 120 | 265 |
| Medical and Health | Nursing | 53 | 69 | 122 | | | | 53 | 69 | 122 |
| | Health Officer | 49 | 25 | 74 | | | | 49 | 25 | 74 |
| | sub total | 102 | 94 | 196 | | | | 102 | 94 | 196 |
| Over total | | 360 | 239 | 599 | 100 | 26 | 126 | 460 | 265 | 725 |

ዩኒቨርሲቲያችን በማታ ተከታታይ ትምህርት 725 ተማሪዎች (ከነዚህ ውስጥ 36.55% ሴት ተማሪዎች ናቸው) በሶስት ኮሌጆች እና በስምንት ትምህርት ክፍሎች በመማር ላይ ይገኛሉ።

ሰንጠረዥ 7፡ የክረምት ተከታታይ ትምህርት ተማሪዎች (2005 ክረምት)

| College | department | year I | | |
|---|---|---|---|---|
| | | M | F | T |
| Engineering technology | Technical Drawing | 84 | 13 | 97 |
| | Information Technology | 130 | 53 | 183 |
| | sub total | 214 | 66 | 280 |
| Business and economics | Management | 35 | 7 | 42 |
| | sub total | 35 | 7 | 42 |
| medicin and Health | Nursing | 27 | 22 | 49 |
| | sub total | 27 | 22 | 49 |
| Over total | | 276 | 95 | 371 |

ዩኒቨርሲቲያችን ከ2005 ክረምት ጀምሮ የክረምት ትምህርት የጀመረ ሲሆን በ2005 የክረምት ትምህርት ከተከታተሉት 371 ተማሪዎች (ከነዚህ ውስጥ 25.6% ሴት ተማሪዎች ናቸው) ውስጥ በቴክኒካል ድረዊንግ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ትምህርታቸውን ከተከታተሉት አብዛኛዎቹ በትምህርት ሚኒስቴር የተመደቡ ሲሆኑ በነርሲንግ ትምህርታቸውን የተከታተሉት ደግሞ ከክልሉ ጤና ቢሮ ጋር በተደረገው ስምምነት በመማር ላይ የሚገኙ ናቸው። በማኔጅመንት ትምህርታቸውን የተከታተሉ ተማሪዎች ደግሞ በግል በመማር ላይ የሚገኙ ናቸው።

ስለዚህ ዩኒቨርሲቲው በመደበኛ እና በተከታታይ ትምህርት ትምህርታቸውን የተከታተሉት ተማሪዎች በሚከተለው መልኩ ተጠቃልሎ ቀርቧል።

| ዲቪዥን | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|
| መደበኛ | 4328 | 2488 | 6816 |
| ማታ ተከታታይ | 460 | 265 | 725 |
| ክረምት ተከታታይ | 276 | 95 | 371 |
| ድምር | 5064 | 2848 | 7912 |

### 2.2 የአካዳሚክ ሰራተኞች

ዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ በአሁኑ ወቅት በድምሩ 413 መምህራን በተለያዩ የትምህርት መስኮች ያሉት ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 330 በስራ ላይ የሚገኙ የአገር ውስጥ መምህራን ሲሆኑ 21 ደግሞ በስራ ላይ ያሉ የህንድ መምህራን ናቸው። 62 ያህል የዩኒቨርሲቲው መምህራን ደግሞ ለሁለተኛ ዲግሪያቸው እና ለሶስተኛ ዲግሪያቸው በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ። በውጭ አገር ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙት በህንድ 6፤ በኬንያ 1 እና በታይዋን 1 ናቸው። በድምሩ 8 መምህራን በውጭ አገር ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ሲሆን የተቀሩት በሙሉ አገር ውስጥ ትምህርት በመከታተል ላይ የሚገኙ ናቸው። ዩኒቨርሲቲው ካሉት የአገር ውስጥ አካዳሚክ ሰራተኞች ውስጥ 33 (8.4%) የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ፤ 148 (37.7%) የመጀመርያ ዲግሪ ያላቸው ደጋፊ መምህራን፤ 207 (52.8 %) የሚሆኑት ደግሞ በሌክቸረር መአርግ የሚገኙ መምህራን፤ እና የተቀሩት 2 (0.5 %) አሲስታንትና አሶሴት ፕሮፌሰር መአርግ ያላቸው ናቸው። የፆታ ስብጥር በተመለከተ ደግሞ ከጠቅላላው የአገር ውስጥ መምህራን 35 (8.9%) ሴት መምህራን ናቸው።

ሰንጠረዥ 8፤ የአካዳሚክ ሰራተኞች

| ኮሌጅ | TAs | | | BA/BSc | | | MA/MSc/MD | | | A/Aso/Prof | | | Total | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| ኢንጂነሪንግ | 16 | 3 | 19 | 70 | 10 | 80 | 24 | 2 | 26 | | | | 110 | 15 | 125 |
| ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ | 10 | | 10 | 11 | | 11 | 70 | 1 | 71 | 1 | | 1 | 92 | 1 | 93 |
| ህክምናና ጤና ሳይንስ | 2 | | 2 | 12 | 2 | 14 | 17 | 3 | 20 | | | | 31 | 5 | 36 |
| ግብርና እና አከባቢያዊ ሳይንስ | 2 | | 2 | | | | 17 | 2 | 19 | 2 | | 2 | 21 | 2 | 23 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | | | | 9 | 3 | 12 | 27 | 2 | 29 | 1 | | 1 | 37 | 5 | 42 |
| ማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ | | | | 29 | 2 | 31 | 37 | 5 | 42 | | | | 66 | 7 | 73 |
| **ድምር** | **30** | **3** | **33** | **131** | **17** | **148** | **192** | **15** | **207** | **4** | | **4** | **357** | **35** | **392** |
| % | | | | | | | | | | | | | | | |

በስራ ላይ የሚገኙ የአገር ውስጥ መምህራን 330 ሲሆኑ በየትምህርት ክፍሉ ያለው ስርጭት በሰንጠረዥ 9 ተመልክቷል። በስራ ላይ ያሉ 21 የህንድ መምህራን ስላሉ ጠቅላላ በስራ ላይ ያሉ መምህራን ብዛት 351 መሆኑ ነው። በዚህም መሰረት **የመምህር–ተማሪ ጥምርታ** ወይም Teacher-Student Ratio (በስራ ላይ ያሉ መምህራን እና የመደበኛ ተማሪዎች ብቻ በመውሰድ) 19.42 ነው። በትምህርት ላይ ያሉ መምህራንን ጨምረን ከወሰድን እና መደበኛ ተማሪዎችን ብቻ በመጠቀም የሚኖረው የመምህር–ተማሪ ጥምርታ 16.5 ይሆናል። በተከታታይ ትምህርት የሚማሩ ተማሪዎችን በመጨመርና ጠቅላላ መምህራንን (በስራ ላይ እና በትምህርት ላይ ያሉ) በመጠቀም ያለው የመምህራን–ተማሪዎች ጥምርታ 19.15 በስራ ላይ ያሉ መምህራንን በመውሰድ ደግሞ የመምህር–ተማሪ ጥምርታ 22.54 ነው።

ሰንጠረዥ 9፤ በስራ ላይ ያሉ የአገር ውስጥ መምህራን ብዛት

| College | Department | Technical Assistants | | | BA/BSC (Assts.) | | | MA/MSc (Lect.) | | | PhD | Total | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | M | F | T | M | F | T | M | F | Total | M | M | F | T |
| Engineering | Electrical Engineering | 5 | 0 | 5 | 5 | 0 | 5 | 7 | 1 | 8 | 0 | 17 | 1 | 18 |
| | Mechanical Engineering | 2 | 0 | 2 | 10 | 2 | 12 | 5 | 0 | 5 | 0 | 17 | 2 | 19 |
| | Chemical Engineering | 0 | 0 | 0 | 4 | 2 | 6 | 3 | 0 | 3 | 0 | 7 | 2 | 9 |
| | Civil Engineering | 8 | 3 | 11 | 22 | 2 | 24 | 6 | 1 | 7 | 0 | 36 | 6 | 42 |
| | Computer Science | 1 | 0 | 1 | 12 | 2 | 14 | 2 | 0 | 2 | 0 | 15 | 2 | 17 |
| | Information Technology | | | | | | | | | | | 0 | 0 | 0 |
| | **Sub Total** | **16** | **3** | **19** | **53** | **8** | **61** | **23** | **2** | **25** | **0** | **92** | **13** | **105** |
| Natural and Computational Sciences | Biology | 3 | 0 | 3 | 0 | 0 | 0 | 8 | 0 | 8 | 0 | 11 | 0 | 11 |
| | Chemistry | 4 | 0 | 4 | 0 | 0 | 0 | 13 | 0 | 13 | 0 | 17 | 0 | 17 |
| | Mathematics | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 28 | 0 | 28 | 0 | 28 | 0 | 28 |
| | Physics | 2 | 0 | 2 | 0 | 0 | 0 | 8 | 1 | 9 | 1 | 11 | 1 | 12 |
| | Statistics | 0 | 0 | 0 | 3 | 0 | 3 | 4 | 0 | 4 | 0 | 7 | 0 | 7 |
| | Geology | 0 | 0 | 0 | 3 | 0 | 3 | 1 | 0 | 1 | 0 | 4 | 0 | 4 |
| | Sport Science | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 4 | 0 | 4 | 0 | 5 | 0 | 5 |
| | **Sub Total** | **10** | **0** | **10** | **6** | **0** | **6** | **66** | **1** | **67** | **1** | **83** | **1** | **84** |
| Business and Economics | Accounting and Finance | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 2 | 7 | 1 | 8 | 0 | 8 | 2 | 10 |
| | Economics | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 12 | 1 | 13 | 1 | 13 | 1 | 14 |
| | Management | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 5 | 0 | 5 | 0 | 5 | 0 | 5 |
| | Marketing | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 2 | 0 | 2 |
| | **Sub Total** | **0** | **0** | **0** | **2** | **1** | **3** | **25** | **2** | **27** | **1** | **28** | **3** | **31** |
| Social Sciences and Humanities | English | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 20 | 3 | 23 | 0 | 20 | 3 | 23 |
| | Civics | 0 | 0 | 0 | 18 | 0 | 18 | 2 | 0 | 2 | 0 | 20 | 0 | 20 |
| | Psychology | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 6 | 0 | 6 | 0 | 6 | 0 | 6 |
| | Geography and Environmental Stdies | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 5 | 0 | 5 | 0 | 5 | 0 | 5 |
| | Law | 0 | 0 | 0 | 2 | 0 | 2 | 1 | 1 | 2 | 0 | 3 | 1 | 4 |
| | Sociology | 0 | 0 | 0 | 2 | 0 | 2 | 1 | 1 | 2 | 0 | 3 | 1 | 4 |
| | **Subtotal** | **0** | **0** | **0** | **22** | **0** | **22** | **35** | **5** | **40** | **0** | **57** | **5** | **62** |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **Agriculture and Environmental Science** | Natural Resource Management (SWC) | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 6 | 1 | 7 | 0 | 6 | 1 | 7 |
| | Animal Science | 2 | 0 | 2 | 0 | 0 | 0 | 8 | 0 | 8 | 0 | 10 | 0 | 10 |
| | Plant Science | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 5 | 0 | 5 | 0 | 5 | 0 | 5 |
| | **Subtotal** | **2** | **0** | **2** | **0** | **0** | **0** | **19** | **1** | **20** | **0** | **21** | **1** | **22** |
| **Health and Meidical Sciences** | Nursing | 2 | 0 | 2 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 4 | 0 | 4 |
| | Midwifery | 0 | 0 | 0 | 4 | 1 | 5 | 0 | 0 | 0 | 0 | 4 | 1 | 5 |
| | Health Officer | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| | Medicine | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 2 | 12 | 3 | 15 | 0 | 13 | 4 | 17 |
| | **Subtotal** | **2** | **0** | **2** | **6** | **2** | **8** | **13** | **3** | **16** | **0** | **21** | **5** | **26** |
| **Overall Total** | | **30** | **3** | **33** | **89** | **11** | **100** | **181** | **14** | **195** | **2** | **302** | **28** | **330** |

ከአገር ውስጥ መምህራን በተጨማሪ 21 ህንዳውያን መምህራን በማስተማር ላይ ይገኛሉ። ከህንድ መምህራን ውስጥ አብዛኛዎቹ በህክምናና ጤና ሳይንስ የሚገኙ ናቸው። በየትምህርት ክፍሉ ያሉት የህንድ መምህራን ብዛት በሚከተለው ሰንጠርዥ ተመልክቷል።

ሰንጠረዥ 10. የህንድ መምህራን

| ኪሌጅ | ሌክቸረር | | | ረ/ተ/ፕሮፌሰር | | | ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| ኢንጂነሪንግ | 3 | | 3 | | | | 3 | | 3 |
| ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ | 1 | | 1 | 2 | | 2 | 3 | | 3 |
| ህክምናና ጤና ሳይንስ | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 5 | 5 | 3 | 8 |
| ግብርና እና አከባቢያዊ ሳይንስ | | | | | | | | | |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | | 1 | 1 | 3 | | 3 | 4 | 1 | 4 |
| ማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ | | | | 3 | | | 3 | | 3 |
| **ድምር** | 5 | 3 | 8 | 12 | 1 | 13 | 18 | 4 | 21 |

### 2.3 ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች

ለሶስት አመት ያገለግላል ተብሎ ታምኖበት በተዘጋጀው መዋቅር መሰረት 1186 የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ለመቅጠር ዩኒቨርሰቲው የተፈቀደለት ሲሆን በዚሁም መሰረት በ2005 ከነበሩት የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በተጨማሪ ለ2006 የምንቀበላቸውን አዲስ ተማሪዎች (ማለትም ከአራት ሺ በላይ) መሰረት በማድረግ አራት መቶ ያህል አዲስ ሰራተኞች (አብዛኛዎቹ የተማሪዎች ምግብ ቤት አከባቢ) ለመቅጠር በተያዘው እቅድ መሰረት በርካታ ቅጥሮች ተካሂደዋል። በመዋቅሩ ፈቅደው ያልነበሩ አዳዲስ የስራ መደቦች (ጉልበት ሰራተኛ እና አትክልተኛ ይጠቀሳሉ) እንዲፈቀዱልን ጠይቀንም የተፈቀዱልን በመሆኑ ተጨማሪ ቅጥሮች ተካሂደዋል።

በድምሩ እስከ መጋቢት 30/2006 በዩኒቨርሲቲው የተቀጠሩ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ብዛት በሚከተሉት ሁለት ሰንጠረገሮች የተመለከተውን ይመስላል። ይህ ቁጥር የፅዳት ስራው ወደ ውጭ (outsource) በመውጣቱ ምክንያት በከተማው ትምህርት ጨርሰው ለተደራጁት የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋም እንዲሰጥ ስለተደረገ በዚሁ ማህበር ተቀጥረው በመስራት ላይ የሚገኙትን በርካታ የፅዳት ሰራተኞችን የሚጨምር አይደለም።

ሰንጠረዥ 11. ቋሚ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች

| ተ.ቁ. | ፅህፈት ቤት | እስከ ሰኔ 30 የተቀጠሩ ቋሚ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | ፕረዚደንት ፅ/ቤት | 0 | 3 | 3 |
| 2 | እቅድና ተቋማዊ ማሻሻያ ፅ/ቤት | 2 | 1 | 3 |
| 3 | ሕዝንብና የውጭ ግንኙነት ፅ/ቤት | 2 | 1 | 3 |
| 4 | ውስጥ ኦዲት ፅ/ቤት | 2 | 1 | 3 |
| 5 | ስርኣተ ፆታ ፅ/ቤት | | 1 | 1 |
| 6 | ህግ ፅ/ቤት | 1 | 2 | 3 |
| 7 | ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና መከታተያ ፅ/ቤት | 1 | 1 | 2 |
| 8 | ኣካዳሚክና ምርምር ም/ፕረዚዳንት ፅ/ቤት | 0 | 2 | 2 |
| 9 | ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ | 0 | 5 | 5 |
| 10 | ኢንጂነሪንግ ኮሌጅ | 0 | 9 | 9 |
| 11 | ተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ | 2 | 9 | 11 |
| 12 | ማህበራዊ ሳይንስ ኮሌጅ | 0 | 8 | 8 |
| 13 | ግብርና ኮሌጅ | 0 | 5 | 5 |
| 14 | ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ | 0 | 5 | 5 |
| 15 | ሬጂስትራር | 5 | 20 | 25 |
| 16 | ቤተመፃህፍትና ዶኩመንቴሽን | 59 | 71 | 130 |
| 17 | ኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ማእከል | 4 | 3 | 7 |
| 18 | ኣስተዳደርና ልማት ም/ፕረዚዳንት ፅ/ቤት | 0 | 2 | 2 |
| 19 | ሰው ሃብት ልማት ማእከል | 6 | 9 | 15 |
| 20 | ግዥና ንብረት ኣስተዳደር ዳይሬክቶሬት | 15 | 9 | 24 |
| 21 | የፋይናንስ ኣስተዳደር ዳይሬክቶሬት | 9 | 9 | 18 |
| 22 | መሰረታዊ ኣገልግሎት ማእከል | 139 | 25 | 164 |
| 23 | የተማሪዎች ዲን (ምግብ ቤትና ክሊኒክ ሳይጨምር) | 3 | 3 | 6 |
| 24 | ተማሪዎች ዲን (ምግብ ቤት ሰራተኞች) | 53 | 367 | 420 |
| 25 | የተማሪዎች ዲን (መኝታ ቤትና መዝናኛ) | 15 | 19 | 34 |
| 26 | ተማሪዎች ዲን (ክሊኒክ ሰራተኞች) | 12 | 4 | 16 |
| 27 | የዩኒቨርሲቲ ኢንዳስትሪ ትስስር | 0 | 1 | 1 |
| 28 | የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ | 0 | 2 | 2 |
| 29 | ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት | | 1 | 1 |
| ድምር | | **330** | **598** | **928** |

ከላይ በተመለከተው ሰንጠረዥ እንደሚታየው ዩኒቨርሲቲው እስከ ሰኔ 30/2006 ያሉት ቋሚ የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች 928 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ ወደ ግማሽ የሚሆኑት በተማሪዎች ዲን (ምግብ ቤት፤ መኝታ ቤት፤ ክሊኒክና የመሳሰሉት) አከባቢ የተቀጠሩት ናቸው።

ሰንጠረዥ 12፤ የኮንትራት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች

| ተ.ቁ. | አይነት | እስከ ሰኔ 30 የተቀጠሩ የኮንትራት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | ግንባታ ፕሮጀክት ፅ/ቤት | 8 | 4 | 12 |
| 2 | ጥበቃ | 4 | | 4 |
| 3 | ጉልበት ሰራተኛ | 9 | | 9 |
| 4 | ሾፌር | 2 | | 2 |
| 5 | መኝታ ቤት ተቆጣጣሪዎች | 14 | 5 | 19 |
| **ድምር** | | 37 | 9 | 46 |

የኮንትራት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ጨምሮ ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ዩኒቨርሲቲው እስከ ሰኔ 30/ 2006 ድረስ የነበሩት የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ቁጥር 974 ነው። በፆታ ስብጥር ሲታይ ደግሞ ከጠቅላላው ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ውስጥ 607 ወይም 62.3% ሴት ሰራተኞች ናቸው።

## 3. የተመደበልን ባጀትና አጠቃቀሙ

ዩኒቨርሲቲው ለ2006 የባጀት (የትምህርት) አመት መደበኛ ባጀት እና ካፒታል ባጀት ተፈቅዶለት በእቅድ የያዛቸውን ተግባራቱን ሲያከናውን ቆይቷል።

### 3.1. መደበኛ ባጀት

በባጀት አመቱ መጀመርያ ለ2006 የተፈቀደልን መደበኛ ባጀት በፕሮግራም ባጀት አደላደል መሰረት ለአራት ፕሮግራሞች ማለትም ለፕሮግራም አንድ ወይም ለአስተዳደር ስራዎች (57140060)፤ ለፕሮግራም ሁለት ወይም አካዳሚክ ነክ ስራዎች (53156000)፤ ለፕሮግራም ሶስት ወይም ለጥናትና ምርምር (5190000)፤ እና ለፕሮግራም አራት ወይም ለማህበረሰብ አገልግሎት (1670000) በድምሩ ብር 117156060 የነበረ ሲሆን የባጀት አጠቃቀማችንን በማየት ባቀረብነው የዝውውርና የተጨማሪ ባጀት ጥያቄ መሰረት ተስተካክሎ ተፈቅዶልናል። በዚሁም መሰረት እና ከላይ ለተጠቀሱት አራት ፕሮግራሞች ተስተካክሎ የተፈቀደልን 61347556.79 (ለፕሮግራም አንድ)፤ 52646003.20 (ለፕሮግራም ሁለት)፤ 3560000 (ለፕሮግራም ሶስት)፤ 1352500.01 (ለፕሮግራም አራት) በድምሩ 118906060.00 ነው። ለ2005 ተፈቅዶልን ከነበረ መደበኛ ባጀት (ማለትም 70 ሚልዮን) ጋር ሲነፃፀር የ2006 መደበኛ ባጀት በ48 ሚልዮን ብልጫ ያለው ነው። የመደበኛ ባጀት አጠቃቀማችንን በተመለከተ በባጀት አመቱ (ማለትም እስከ ሰኔ 30/2006) ጥቅም ላይ የዋለው ብር 111114002.17 ነው።አጠቃቀሙ በመቶኛ ሲቀመጥ መጀመርያ ከተፈቀደልን ባጀት ጋር ሲወዳደር 94.85% ሲሆን ተስተካክሎ ከተፈቀደልን ባጀት ሲነፃፀር ደግሞ 93.45% ነው። ቀሪው ገንዘብ ደግሞ በቅድመ ክፍያ መልክ ለተለያዩ ጉዳዮች (ለኮንትራክተሮች እና ለጨረታ ቅድመ ክፍያ እንዲከፈል ተደርጓል። በየባጀት አርእስቱ የነበረው የባጀት አጠቃቀም *በተጨማሪ ማብራርያ 1 (Appendix 1) ሰንጠረዥ ሀ* በዝርዝር ማየት ይቻላል። በአጠቃላይ ሲታይ በአመቱ የነበረው የመደበኛ ባጀት አጠቃቀም አጥጋቢ እንደነበረ መገንዘብ ይቻላል።

ግዥዎችን በዋናነት ያካሄድነው ባወጣናቸው አምስት የግልፅ ጨረታዎች እንዲሁም ሲሆን ከዚሁም በተጨማሪ፤ውሱን ጨረታዎች የፕሮፎርማ እና የቀጥታ ግዥዎችን ተጠቅመናል። በ2006 ዝርዝር እቅድ በተቀመጠው መሰረት ከ4000 በላይ አዲስ ተማሪዎችን መቀበል ስለነበረብን ለተማሪዎቹ አቀባበል ይረዳ ዘንድ የተለያዩ እንደነ አልጋ፤ ወንበር፤ ሎከር ግዥዎችን ማካሄድ፤ እንዲሁም ለቢሮ አገልግሎት የሚውሉ ወንበሮች፤ ጠረጴዛዎች፤ እና ሌሎች ማቴርያሎች፤ በተጨማሪም ለቢሮ አገልግሎት የሚውሉ ማቴርያሎች (ወረቀት፤ ኮምፕዩተር፤ ወዘተ)፤ እና ለተማሪዎች ምግብ ቤት አገልግሎት የሚውሉ የምግብ ግብአቶች እና መሳርያዎች (የዳቦ መጋገርያ ማሽን፤ ወፍጮ፤ የመጠባበቅያ ጀነሬተር) ግዥዎች ሲካሄዱ ቆይተዋል። የተማሪዎች ሎከሮች (የልብስ ማስቀመጫ ካፕቦርድ) አመቺ በሆኑ ዶርሚተሪዎች (ትናንሾቹ ዶርሚተሪዎች) ውስጥ የግንባታ ስራውን በሚሰሩት ኮንትራክተሮች አመካኝነት ቋሚ ሎከሮች እንዲሰሩ በመደረጉ የተሻለ ጥራት ያላቸው

የልብስ ማስቀመጫ ሎከሮች ሊሰሩ ችለዋል። ከዚሁም በተጨማሪ ግቢውን ባጠቃላይ በኔትወርክ ለማገናኘት የሚያስችለን ጨረታ ወጥቶ የጨረታ ትንተና አልቆ እና በግዥ አፅዳቂ ፀድቆ የገንዘቡ መጠን 58 ሚልዮን የሚደርስ በመሆኑ (እና በግዥ መመርያው ከሚፈቀደው በላይ ስለሆነ) ውል ለማሰር እንዲፈቀድልን ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ጥያቄ አቅርበን ስለተፈቀደልን ውሉን ያሰርን ሲሆን ስራው (የዳታ ሰንተር ተከላ፤ የውስጥ ለውስጥ ፋይበር ኦፕቲክ መስመር ዝርጋታ፤ ስማርት ክላስ፤ አይፒ ቴሌፎኒ፤ እና ሌሎች ስራዎችን የሚያጠቃልል ነው) በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ይጠበቃል። ከዚሁም በተጨማሪ በባጀት አመቱ የኢንተርኔት አገልግሎትን ወደየቢሮው ለማዳረስ በተያዘው እቅድ መሰረት የአካዳሚክ ክንፉን ትኩረት በማድረግ የኔትወርክ ዝርጋታ የተከናወነ ሲሆን የሞቶሮላ ገመድ አልባ አገልግሎት ተተክሎ አገልግሎት ላይ የዋለ ሲሆን ወደየፅህፈት ቤቱ የኢንተርኔት አገልግሎት ለማዳረስ ተችሏል። በዚሁም መሰረት በአንድ የኮምፕዩተር ላቦራቶሪ ብቻ ይሰጥ የነበረው የኢንተርኔት አገልግሎት ወደየፅህፈት ቤቱ ለማዳረስ ተችሏል።

ሰንጠረዥ 13. ለ2006 የተፈቀደ እና በአመቱ ጥቅም ላይ የዋለ መደበኛ ባጀት

| የባጀት መደብ | መጀመርያ የተፈቀደ | ተስተካክሎ የተፈቀደ | እስከ ሰኔ 30 ወጪ የተደረገ | አጠቃቀም በመቶኛ (መጀመርያ ከተፈቀደው) | አጠቃቀም በመቶኛ (ተስተካክሎ ከተፈቀደው) |
|---|---|---|---|---|---|
| 6100 | 26491350.00 | 39762863.99 | 38570580.76 | 145.60 | 97.00 |
| 6200 | 76072650.00 | 66216136.01 | 59021037.28 | 77.59 | 89.13 |
| 6300 | 12501060.00 | 12151060.00 | 11796496.44 | 94.36 | 97.08 |
| 6400 | 2076000.00 | 776000.00 | 1725887.69 | 83.14 | 222.41 |
| **ድምር** | 117141060.00 | 118906060.00 | 111114002.17 | **94.85** | **93.45** |

### 3.2. ካፒታል ባጀት

ለ2006 የስራ ዘመን የተፈቀደልን የካፒታል ባጀት ልክ እንደ መደበኛ ባጀቱ በፕሮግራም ባጀት መሰረት ሲሆን የተፈቀደልን ለስድስት ፕሮግራሞች ነው። በዚሁም መሰረት በባጀት አመቱ መጀመርያ ላይ ተፈቅዶልን የነበረው የካፒታል ባጀት 283943120 ነው። ሆኖም የባጀት አጠቃቀማችን ከተፈቀደው በላይ ስለነበረ ተጨማሪ ባጀት እንዲመደብልን ጠይቀን (የባጀት ማዛወር ስራም ተሰርቶ) ተስተካክሎ የተፈቀደልን የካፒታል ባጀት 268344793.77 (ለፕሮግራም አንድ)፤ 61685810.59 (ለፕሮግራም ሁለት)፤ 19835681 (ለፕሮግራም ሶስት)፤ 7460500 (ለፕሮግራም አራት)፤ 4698036.64 (ለፕሮግራም አምስት)፤ 22275511.07 (ለፕሮግራም ስድስት) በድምሩ 384300333.07 ነው። ተስተካክሎ የተፈቀደልን ባጀት መጀመርያ ተፈቅዶልን ከነበረ በአንድ መቶ ሚልዮን ያህል ብልጫ ያለው ሲሆን ከዚሁ ውስጥ በባጀት አመቱ ወጪ የተደረገው ብር 372357146.33 ነው። በመቶኛ ሲገለፅ የባጀት አጠቃቀማችን መጀመርያ ተፈቅዶልን ከነበረው ባጀት 131.14% ሲሆን ተስተካክሎ ከተፈቀደልን ደግሞ 96.9% ነው። ቀሪው ገንዘብ ደግሞ በቅድመ ክፍያ መልክ ለተለያዩ ስራዎች ወጪ የተደረገ ነው። የካፒታል ባጀት አጠቃቀማችን አጥጋቢ እንደነበረ ከቀረቡት አሃዞች መገንዘብ ይቻላል። በየባጀት ርእሱ የነበረው አጠቃቀም ደግሞ ***በተጨማሪ ማብራርያ 1 (Appendix 1) ሰንጠረዥ1*** ላይ በዝርዝር ቀርቧል።

የካፒታል ባጀት በዋናነት የምንጠቀምበት ለግንባታ ነክ ስራዎች ሲሆን በተጨማሪም ለውጭ መምህራን ደምወዝ እና ለዩኒቨርሲቲው አስፈላጊ የሆኑ የካፒታል እቃዎች ግዥዎች እንጠቀምበታለን።

ሰንጠረዥ 14. ለ2006 የተፈቀደ ካፒታል ባጀት እና በአመቱ የነበረው አጠቃቀም

| የሂሳብ መደብ | መጀመርያ የተፈቀደ | ተስከታክሎ የተፈቀደ | እስከ ሰኔ 30 ወጪ የተደረገ | አጠቃቀም በፐርሰንት (መጀመርያ ከተፈቀደው) | አጠቃቀም በመቶኛ (ተስከካክሎ ከተፈቀደው) |
|---|---|---|---|---|---|
| 6100 | 4865900.00 | 7710689.85 | 7641219.93 | 157.04 | 99.10 |
| 6200 | 18756860.00 | 5899290.02 | 3527010.82 | 18.80 | 59.79 |
| 6300 | 260320360.00 | 370690353.20 | 361188915.58 | 138.75 | 97.44 |
| 6400 | 0.00 | 0.00 | 0.00 | | |
| **ድምር** | **283943120** | **384300333.1** | **372357146.3** | **131.14** | **96.89** |

### 3.3. የግንባታ ስራዎች አፈፃፀም

ዩኒቨርሲቲው በአምስት አመታት ውስጥ አስራ አምስት ሺ ተማሪዎችን ሊያስተናግድ ይችላል በሚል እሳቤ ነው የግንባታ ስራዎች በመሰራት ላይ ያሉት። የግንባታ ስራዎች ሲባል የህንፃ ግንባታ እና የመሰረተ ልማት ስራዎች ተብሎ ለሁለት የሚከፈል ሲሆን የህንፃ ግንባታው በአምስት ዙሮች የሚካሄድ ሆኖ በድምሩ 190 ያህል ብሎኮች ይኖሩታል። የመሰረተ ልማት ስራዎች ደግሞ የውሃ፤ የመንገድ፤ የፍሳሽና፤ የኤሌክትሪክ ስራዎችን የሚያጠቃልል ነው። በዚሁም መሰረት አንደኛ ዙር እና ሁለተኛ ዙር የህንፃ ግንባታ ስራዎች በወሳኝ መልኩ ተጠናቀዋል። ከአንደኛው ዙር እስካሁን ድረስ ያልተጠናቀቀው አንድ ኮንትራተር ከያዘው ውስጥ የተማሪዎች መዝናኛ ህንፃ ሲሆን ሌሎች ተጠናቀው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። የአንደኛው ዙር በድምሩ 48 ብሎኮችን የያዘ ሲሆን ከላይ ከተጠቀሰው የተማሪዎች መዝናኛ (የተማሪዎች ላውንጅ) በስተቀር ሌሎቹ የተጠናቀቁ ናቸው።

የሁለተኛው ዙር ህንፃ ግንባታ 2004 ሰኔ አከባቢ የተጀመረ ሆኖ በድምሩ (ማለትም የልብስ ማጠብያ እና ትራንስፎርመር ቤቶችን ጨምሮ) 67 ሲሆኑ ዋና ዋና ብሎኮች ግን 54 ናቸው። ግንባታዎቹ በ33 ኮንትራክተሮች ነው የተሰሩት። የሁለተኛው ዙር ብሎኮች በወሳኝ መልኩ ዝግጁ በመሆናቸው ምክንያት ዩኒቨርሲቲው ባቀደው መልኩ በ2006 የትምህርት ዘመን ከ4000 በላይ ተማሪዎችን ለመቀበል አስችሎታል። በተጨማሪ ማብራር 2 (Appendix 2) ሰንጠረዥ ሀ በዝርዝር እንደተመለከተው እስከ ሰኔ 30/2006 ድረስ የነበረው የሁለተኛው ዙር ህንፃ ግንባታዎች አፈፃፀም በድምሩ 97.91% ደርሷል። ከአፈፃፀሙ መረዳት እንደሚቻለው የሁለተኛው ዙር ግንባታ ስራዎች ከጥቂት ህንፃዎች በስተቀር ሌሎቹ ተጠናቀው ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው። እንዚህ ህንፃዎች ስለደረሱልም ነው በ2006 ከ4000 በላይ አዲስ ተማሪዎችን ተቀብለን ማስተናገድ የቻልነው። የተቀሩትም ቢሆን በሚቀጥሉት ወራተ ውስጥ ተጠናቀው ለ2007 ተማሪዎች ቅበላ የሚደርሱ ይሆናል። በአንድ ኮንትራክተር እየተሰራ ያለው እና የውሃ መስመር ዝርጋታ፤ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ፤ እና የፍሳሽ መስመር ዝርጋታን የሚያጠቃልለው የመሰረተ ልማት (የትራንስፎርመር ቤቶችን ጨምሮ) የመጀመርያው ዙር ስራም በወሳኝ መልኩ ተጠናቆ ጥቅም እየሰጠ ይገኛል። ዝርዝሩን በተጨማሪ ማብራርያ 2 (Appendix 2) ሰንጠረዥ ለ ማየት ይቻላል።

ለ2007 አዲስ ተማሪዎች ቅበላ የሚሆን የሶስተኛ ዙር ግንባታዎች ደግሞ ሐምሌ 2005 አከባቢ ተጀምረው አሁን እቀየጠሉ ናቸው። በመሰራት ላይ የሚገኙት የሶስተኛ ዙር ህንፃዎች (ስድስት የማጠብያ ክፍሎችን ወይም Washing Basin ጨምሮ) 31 ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ ብሎኮች 25 ናቸው። ከነዚህ ብሎኮች በተጨማሪ አንድ መለስተኛ የስፖርት ሜዳ እየተሰራ ይገኛል። በሶስተኛ ዙር ግንባታ በመሳተፍ ላይ ያሉት ኮንትራክተሮች 17 ናቸው። የሶስተኛ ዙር ግንባታ ለ2007 አዲስ ተማሪዎች ቅበላ ይደርሳል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን እስከ ሰኔ 30/2006 ያለበት የፍፃሜ ደረጃ 88.96% ነው። የያንዳንዱ ግንባታ የፍፃሜ ደረጃ ዝርዝር በተጨማሪ ማብራርያ 2 (Appendix 2) ሰንጠረዥ ሐ ማየት ይቻላል። የሶስተኛ ዙር ግንባታ እነዚህን ብቻ የሚያካተት ባለመሆኑ የተቀሩት ወደ 12 የሚሆኑ ብሎኮች ደግሞ በምውፃእ ወርቂ ግቢ ለማሰራት እቅድ ተይዞ የነበረ ሲሆን እስካሁን ከቦታ ካሳ ጋር እና ከዲዛይን ስራዎች በተያያዙ ጉዳዮች ምክንያት

ግንባታው ያልተጀመረ ቢሆንም ቦታውን የመከለል (የማጠር) ስራ ግን እየተሰራ ይገኛል። ዩኒቨርሲቲው ለ2007 ብዛት ያላቸው (ቀደም ብሎ ዩኒቨርሲቲው 4500 ያህል አዲስ ተማሪዎችን ለመቀበል አቅዶ የነበረ ቢሆንም ትምህርት ሚኒስቴር በመሰናዶ ትምህርት ቤቶች ፈተና ላይ የቀረቡት ተማሪዎች ብዛታቸው ከፍተኛ በመሆኑ ተጨማሪ ተማሪዎችን እንድንቀበል በጠየቀን መሰረት ቁጥሩን ወደ 5000 አሳድገነዋል) ተጨማሪ አዲስ ተማሪዎችን ለመቀበል እቅድ የያዘ ሲሆን የሶስተኛው ዙር ግንባታ አፈፃፀም በጥሩ ደረጃ ስለሚገኝ የተጠቀሰውን የተማሪ ቁጥር ለመቀበል ያስችለናል ተብሎ ይታመንበታል። ሆኖም ተማሪዎቹን ለመቀበል ያስችለን ዘንድ ከላይ ከተቀመጡት የህንፃ ግንባታዎች በተጨማሪ አንድ የመመገብያ አዳራሽ፣ ሁለት የእንጀራ መጋገርያ ቤቶች፣ እና ሁለት የዎርክሾፕ አዳራሾች ተፈላጊነታቸው ስለታመነበት ከሚያዝያ 2006 ጀምሮ የነዚህ ህንፃዎች ግንባታ በዋናው ግቢ እንዲጀመር ተደርጓል። የአነስተኛ እና ጥቃቅን ድርጅቶች ተሳትፎን በተመለከተ በግንባታው ስራ ባጠቃላይ **43 የጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች** በግንባታው ስራ (ማለትም በብሎኬት 12፣ በፕሪካስት 4፣ በኮብልስቶን 4፣ በብረታ ብረት 13፣ በኤሌክትሪ 4፣ በጫኝና አውራጅ 2) በመሳተፍ ላይ ይገኛሉ።

የመሰረተ ልማት ግንባታ አካል የሆነው የፍሳሽ ማጣርያ ፕላንት (Waste Water Treatment Plant) ዲዛይኑ አልቆ ከደረሰን በኋላ አሁን የመሰረተ ልማት ግንባታ በመስራት ላይ ያለው ድርጅት እንዲይዘው በማድረግ ውል የታሰረ ሲሆን ተጨማሪ በታ ያስፈልግ ስለነበረ ለምስራቃዊ ዞን አስተዳደር ተጨማሪ ቦታ እንዲሰጠን ጥያቄ አቅርበን በዋናው ግቢ ተጨማሪ ቦታ ተሰጥቶን የካሳ ግምት ተሰርቶ ተሰርቶለት ክፍያ ተደርጎበት የግንባታ ስራው እየተሰራ ይገኛል። ከቦታው መልቀቅ ያለባቸው ነዋሪዎች ተለዋጭ ቦታ ካልተሰጠን አንለቅም የሚል ጥያቄ ስላቀረቡ ቦታ እስኪሰጣቸው ድረስ የራሱ ጊዜ ወስዶ የነበረ እና ከካሳ ጥያቄ ጋር የተነሱ ክርክሮች ስለነበሩ የግንባታው ስራ በሙሉ ሃይል መጀመር አስቸጋሪ የነበረ እና መዘግየት የታየበት ቢሆንም አሁን ግን የግንባታው ስራ በሙሉ ሃይል እየተከናወነ ይገኛል። የዚህ ፕላንት ግንባታ ወደ 180 ሚልዮን አከባቢ ይፈጃል ተብሎ ግምት የተያዘለት እና ለማጠናቀቁም ከአንድ አመት በላይ የሚወስድ ስለሆነ በ2007 መጨረሻ አከባቢ ሊጠናቀቅ እንደሚችል ታሳቢ ተደርጓል።

ዩኒቨርሲቲው ከዋናው የአስፋልት መንገድ (ማለትም ከውቅሮ-ዛላምበሳ የሚሄደው እና በቻይና ኩባንያ ተሰርቶ በመጠናቀቅ ላይ ካለው የመንገድ ፕሮጀክት) 500 ሜትር ያህል ገባ ብሎ የሚገኝ ስለሆነ እና መንገዱ የዩኒቨርሲቲው ዋና መውጫና መግቢያ መንገድ ሆኖ በማገልገል ላይ የሚገኝ ስለሆነ ይሄንን መንገድ በአስፋልት ለማሰራት ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ጋር በመነጋገር በቻይናው ኩባንያ እንዲሰራ ስምምነት ስምምነት ተደርሶበት እና ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እንዲፈቅድልን ጥያቄ አቅርበን በተፈቀደልን መሰረት ግንባታው በጥሩ ሁኔታ እና በወቅቱ ተጠናቆ ጥቅም እየሰጠ ይገኛል።

በአጠቃላይ በዩኒቨርሲቲው የሚደረጉ የግንባታ ስራዎች አፈፃፀም በውጤታማነቱ የሚጠቀስ ነው። በተመሳሳይ ደረጃ ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ሲታይ በአብነትነት የሚገለፅ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ለውጤቱ ጥሩ መሆን አስተዋፅኦ ያደረጉ በዩኒቨርሰቲው በኩል የሚደረጉት ዋና ዋና ተግባራት በሶስት ከፍሎ ማየት ይቻላል፤

1. የግንባታ ስራውን በተመለከተ በግንባታ ፕሮጀክት ፅ/ቤት በተለይና ባጠቃላይም በአመራሩ በኩል ጥብቅ የክትትል ስራ ይደረጋል፤ ተደጋጋሚ ውይይቶች ከኮንትራክተሮች ጋር በማድረግ የዩኒቨርሰቲው እቅድ መሰረት ባደረገ መልኩ ኮንትራክተሮች ግንባታዎችን እንዲያፋጥኑ ስምምነት ይደረስበታል፤ ለሚያጋጥሙ ችግሮች ደግሞ መፍትሄ ይቀመጥላቸዋል።
2. ኮንትራክተሮች በአፈፃፀማቸው ደረጃ ይወጣላቸዋል፤ ያላቸው ደረጃ ለሁሉም ኮንትራክተሮች በስብሰባ ይነገራቸዋል፤ ቅሬታ ያላቸው እንዲያቀርቡ እድል ይሰጣቸዋል። በተቀመጠላቸው የአፈፃፀም ደረጃ ደግሞ ተጨማሪ ስራ እንዲሰጣቸው ይደረጋል። ዝቅተኛ አፈፃፀም ያላቸው ተጨማሪ ስራ ይከለከላሉ።
3. በተዘረጋው አሰራር መሰረት አስፈላጊውን የሚያሟሉ ኮንትራክተሮች የፈጣን የክፍያ ስርአት ተጠቃሚ ይሆናሉ።

## 4. የእቅድ አፈፃፀም

ዩኒቨርሲቲው ስራ ከጀመረበት ከ2004 ጀምሮ በቁልፍ ተግባር ዙርያ አመታዊ ዝርዝር እቅድ በማዘጋጀትና በእቅዱ ላይ መግባባት በመድረስ ነው ስራዎቹን በማከናወን ላይ የሚገኘው። በየአመቱ ደግሞ መሪ ቃል (motto) እየተዘጋጀ በዚሁ መሪ ቃል በመሰባሰብ የአመቱን እቅድ በመፈፀም እና የእቅድ አፈፃፀምም በስድስት ወር እና በአመቱ መጨረሻ ጠቅላላው የዩኒቨርሲቲ መምህራን እና ሰራተኞች በሚገኙበት መድረክ እንዲገመገም ይደረጋል። በዚሁም መሰረት በ2004 የነበረው መሪ ቃል " ነባር ዩኒቨርሲቲዎች ከደረሱበት ደረጃ ተነስተን ወደፊት እንጓዝ" የሚል ሲሆን በ2005 ደግሞ "መጠናከርና መስፋፋት" የሚል መሪ ቃል ነበረን።

የ2006 የስራ ዘመን ቁልፍ ተግባር "**ሰላማዊ መማር ማስተማር እና መልካም አስተዳደር የሰፈነበት ዩኒቨርሲቲ ይሆን ዘንድ የትምህርት ልማት ሰራዊት ለመገንባት ሁሉን አቀፍ እንቅስቃሴዎችን ማከናወን**" የሚል ሲሆን በዚህ ቁልፍ ተግባር ስር የአመቱ መሪ ቃል ደግሞ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በየደረጃው እና በተከታታይነት በእቅድ፤ በአፈፃፀምና በግምገማ በሚያሳትፍ መልኩ የተቀረፀ ሆኖ መሪ ቃሉ **በጋራ እናቅዳለን፤ በጋራ እንፈፅማለን፤ በጋራ እንገመግማለን** ወይም **We shall plan, implement, and evaluate in unison** የሚል ነው።

በዚሁም መሰረት የ2005 ስራ አፈፃፀም ሰኔ 29/2005 ጠቅላላ መምህራንና ሰራተኞች ባሳተፈ መልኩ ከተገመገመ በኋላ የ2006 የዝግጅት ምእራፍ ላይ ዝርዝር እቅዱ ተዘጋጅቶ በየደረጃው ውይይት ተደርጎበት መስከረም 2006 ላይ ጠቅላላ መምህራንና ሰራተኞች በተሳተፉበት መድረክ ውይይት ተደርጎበት ስምምነት ከተደረሰበት በኋላ በዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ቦርድ ፀድቆ ለተግባር ምእራፍ ዝግጁ እንዲሆን ተደርጓል። በአፈፃፀም ምእራፍ ላይ በስድስት ወራት በዩኒቨርሲቲው የተከናወኑት ዋና ዋናዎቹ ተግባራት ደግሞ ከእቅዱ ጋር በማነፃፀር በሰንጠረዥ መልክ ቀርቧል። በተያዘው እቅድ መሰረት የስድስት ወራት ስራ አፈፃፀሙ በመላው የዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ ጥር 21/2006 በተካሄደው የአንድ ቀን የግምገማ መድረክ እንዲገመገም ተደርጓል። አመታዊ የአፈፃፀም ግምገማ ደግሞ ሰኔ 28/2006 የዩኒቨርሲቲው መምህራንና ሰራተኞች በተገኙበት የአንድ ቀን ውይይት ተደርጎበታል። በአመቱ የተከናወኑ ዋና ዋና ስራዎች አጠር ባለ መልኩ እንደሚከተለው የቀረቡ ሲሆን ዝርዝረ አፈፃፀሙ ደግሞ በሰንጠረዥ መልክ ተቀምጧል።

### 4.1. መማር ማስተማር

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው በተያዘው እቅድ መሰረት 4419 አዲስ ተማሪዎች ለ2006 የትምህርት ዘመን የተመደቡልን ሲሆን ነባር ተማሪዎችን ጨምሮ በአመቱ የአንደኛ ሰሚስተር 7291 መደበኛ ተማሪዎች ተመዝግበው ትምህርታቸውን የተከታተሉ ሲሆን በሁለተኛው ሰሚስተር ደግሞ ተመዝግበው ትምህርት የተከታተሉት መደበኛ ተማሪዎች ቁጥር 6816 ነው። በአንደኛ ሰሚስተር ከነበሩት ተማሪዎች ውስጥ 522 ተማሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ትምህርት ያቋረጡ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ አብዛኞዎቹ (ማለትም 244 ተማሪዎች ወይም ከጠቅላላው ተማሪዎች 3.34%) በራሳቸው ምክንያትና ዩኒቨርሲውን ሳያስፈቅዱ ያቋረጡ ሲሆን በትምህርት ድክመት ምክንያት እንዲያቋርጡ የተገደዱት ደግሞ 181 ተማሪዎች ወይም ከጠቅላላው ታማሪዎች 2.48% ናቸው።

በ2006 የትመህርት ዘመን ትምህርቱን ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ ሰብአዊና ቁሳዊ ዝግጅቶች ከሞላ ጎደል ተጠናቀው ነው ተማሪዎች እንዲገቡ የተደረገው። የዝግጅት ምእራፉ ማጠቃለያ የሆነው ደግሞ መላው የዩኒቨርሲቲ መምህራንና ሰራተኞች የተገኙበት የሁለት ቀን ውይይት በሃይማኖች አክራሪነት እና በዩኒቨርሲቲው እቅድ ዙርያ ተደርጎበታል። ከዚሁም በተጨማሪ በተመሳሳይ ርእሶች ዙርያ መላው ተማሪዎች የተገኙባቸው መድረኮች ተዘጋጅተው የሁለት ቀን ውይይቶች ተካሂደዋል። ለመምህራን ደግሞ በትምህርት ጥራት፤ ተማሪ ተኮር የትምህርት ስርአት፤ ተከታታይ ምዘና (Continuous Assessment)፤ ቋሚ መስፈርት ያደረገ የነጥብ አሰጣጥ ስርአት (Criterion Referenced Grading)፤ ሞዱላር የማስተማር ስርአት እንዲሁም የጥራት ምዘና (Quality

Rating) በሚሉ ርእሶች ዙርያ ከመቐለ ዩኒቨርሲቲ፤ ከሃረማያ ዩኒቨርሲቲ፤ እና ከከፍተኛ ትምህርት ተገቢነትና ጥራት ኤጀንሲ (Higher Education Relevance and Quality Agency) በመጡ ባለሞያዎች የአራት ቀን ስልጠና ተሰጥቷል።

የአመቱ ቁልፍ ተግባር የትምህርት ልማት ሰራዊት ግንባታ መሆኑ በተያዘው እቅድ መሰረትም በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀው የትምህርት ልማት ሰራዊት ግንባታ ማንዋል መሰረት ዩኒቨርሲቲያችን የራሱን ማንዋል አዘጋጅቶና በማንዋሉ ላይ በዩኒቨርሲቲ ካውንስል ደረጃ እና በየትምህርት ክፍሉ ደረጃ ውይይቶችን በማድረግ ወደ ትግበራ ተገብቷል። በዚሁም መሰረት የተማሪዎች፤ የመምህራንና የሰራተኞች የአንድ ለአምስት ቡድኖች እንደአዲስ እንዲቋቋሙ ተደርጎ የተሻለ ውጤት ተገኝቶበታል። በአንደኛ ሰሚስተር የታዩት ክፍተቶች በሁለተኛ ሰሚስተር እንዲሻሻሉ ተደርጎ በተለይ በተማሪዎች አከባቢ በጥሩ ሁኔታ ሊገለፅ የሚችል የተማሪዎች የአንድ ለአምስት መረቦች (Cooperative Learning Teams) ተቋቁመው የተሻለ ውጤት ያለው ስራ ተሰርቷል። በየኮሌጁ የተቋቋሙት የአንድ ለአምስት ቡድኖች በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርበዋል፤

ሰንጠረዥ 15፤ በሁለተኛ ሰሚስተር የነበሩት የተማሪዎች የአንድ ለአምስት እና የልማት ቡድኖች

| ኮሌጅ | የአንድ ለአምስት ቡድኖች (Cooperative Learning Teams) | | | | የልማት ቡድኖች (Development Teams) |
|---|---|---|---|---|---|
| | አንደኛ አመት | ሁለተኛ አመት | ሶስተኛ አመት | ድምር | |
| ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ | 347 | 196 | 53 | 596 | 59 |
| ተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ | 83 | 62 | 29 | 174 | 25 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | 105 | 75 | 34 | 214 | 25 |
| ማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ | 71 | 32 | 11 | 114 | 15 |
| ግብርናና አከባቢ ሳይንስ | 31 | 19 | 0 | 50 | 6 |
| ህክምናና ጤና ሳይንስ | 34 | 29 | 0 | 63 | 6 |
| ድምር | 671 | 413 | 127 | 1211 | 136 |

ከላይ በሰንጠረዥ መልክ እንደተቀመጠው በሁለተኛ ሰሚስተር በድምሩ 1211 የአንድ ለአምስት የተማሪዎች ቡድኖች ተቋቁመው ውጤታማ ስራ ሰርተዋል። የተማሪዎች አንድ ለአምስት ቡድኖችን የሚከታተሉ እና የሚደግፉ የክፍል ደጋፊ መምህራን (mentors) እንዲመደቡ ተደርገዋል። አፈፃፀሙን በተመለከተ በአንደኛ ሰሚስተር መጨረሻ ላይ የተሻለ አፈፃፃም ያላቸው እና የደከመ አፈፃፀም ያላቸው ተብለው በሰኔት ደረጃ ተገምግሞ በሁለተኛ ሰሚስተር የተሻለ ስራ መሰራት እንዳለበት ስምምነት ተደርሶበታል። በኮሌጅ ደረጃ የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ እና የግብርናና አከባቢ ጥናት ኮሌጅ ሲሆኑ ከተቀሩት ኮሌጆች ውስጥ በማህበራዊ ሳይንስ እና በህክምና ኮሌጆች የሚገኙ አንዳንድ ትምህርት ክፍሎች የተሻለ እንቅስቃሴ ያደረጉ ይገኙበታል። በተፈጥሮ ሳይንስ እና በኢንጂነሪንግ ኮሌጅ ግን የአንድ ለአምስት እንቅስቃሴዎች ደከም ብለው የተገኙ ስለሆነ ለሁለተኛ ሰሚስተር በተጠናከረ ሁኔታ መሰራት እንዳለበት ስምምነት ተደርሶበታል። የአስተዳደር ክፍሉ በተመለከተ ደግሞ የተሻለ እንቅስቃሴ ያሳዩት የምግብ ቤት አከባቢ እና የጥበቃ ሰራተኞች ናቸው። በሌሎቹ ክፍሎች እንቅስቃሴው የተጀመረ ቢሆንም በሚፈለገው መልኩ እንዲሰሩ የበለጠ ክትትል የሚፈልጉ ሆነው ተገኝተዋል። በአጠቃላይ ሲታይ የተማሪዎች ቡድኖች የተሻለ እንቅስቃሴ ያሳዩ ሲሆን በመምህራንና ሰራተኞች አከባቢ የነበረው አፈፃፀም ግን ዝቅተኛ እንደሆነ ታይቷል። የተማሪዎች አንድ ለአምስት ስራዎችን ለመደገፍ በሁለቱም የዩኒቨርሲቲው ቤተመፃህፍቶች ሰፋፊ አዳራሾችን በመለየት እነዚህ ቡድኖች እንዲጠቀሙበት እየተደረገ ነው። በድምሩ ሲታይ ቀደም ብለው ይቀርቡ የነበሩ ተቃውሞዎች በወሳኝ መልኩ የቀነሱበት ደረጃ ላይ የተደረሰ ሲሆን በተጀመሩት ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች በማጀብ በተለይ በሁለተኛው ሰሚስተር በሁሉም ኮሌጆች የተሻለ ስራ ተሰርቶበታል።

በአንደኛ ሰሚስተር መጨረሻ ላይ ከላይ በተቀመጠው መልኩ በዩኒቨርሲቲው ሰኔት ከተገመገመ በኋላ እና በጉዳዩ ላይ በዩኒቨርሲቲው ቦርድ ሰፋ ያለ ውይይት ከተደረገበት በኋላ የተደረጉት ጅማሮዎች ጥሩ ቢሆኑም የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው በበለጠ እንዲጠናከሩ ደከም ብለው የነበሩት ደግሞ የሌሎችን ልምድ መሰረት በማድረግ የተጠናከረ እንቅስቃሴ እንዲደረግ በቦርዱ አቅጣጫ ተሰጥቶበታል። በዚሁም መሰረት በሁለተኛው ሰሚስተር የተጠናከረ እንቅስቃሴ በማድረግ የተሻለ ውጤት ተገኝቶበታል። የተለያዩ መድረኮችን በመፍጠር ተጨማሪ የመግባባት ስራዎች የተደረጉ ሲሆን በአጠቃላይ ሲታይ በዩኒቨርሲቲው ልማታዊ ሰራዊትን ለመገንባት ምቹ ሁኔታ የተፈጠረ ሲሆን በሞዴልነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ስራዎችም (ለምሳሌ በማኔጅመንት እና በሳይኮሎጂ ትምህርት ክፍሎች) ታይተዋል። በአንደኛ ሰሚስተር ደከም ያለ እንቅስቃሴ የነበራቸው ኮሌጆች በሁለተኛው ሰሚስተር የተሻለ እንቅስቃሴ አሳይተዋል።

## 4.2. ምርምር እና ህብረተሰብ አገልግሎት

የምርምር ስራዎችን በተመለከተ በ2005 ለውድድር ከቀረቡት 71 የምርምር ፕሮፖዛሎች 23 ተመርጠው እንዲሰሩ ባጀት የተመደበላቸው መሆኑ የሚታወስ ነው። ከነዚህም በተጨማሪ በሂሳብ እና በሳይንስ ትምህርቶች ጥራት ዙርያ የሚያተኩር እና ከክልሉ የትምህርት ቢሮ እና በክልሉ ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ጥናት እንዲካሄድ በተያዘው እቅድ መሰረት ከዩኒቨርሲቲው ባጀት ተመድቦለት የተሰራ የምርምር ስራም ነበር። ከክልሉ የፋይናንስና ፕላን ቢሮ እና ከግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ በመተባበር የተሰራው የተቀናጀ ቤተሰብ ተኮር ፓኬጅ ፕሮግራም እና ውጤቱ የሚያተኩር ሆኖ በክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ስፖንሰር አድራጊነት የተሰራው የምርምር ስራም ተከናውኗል። ፀድቀው ሲሰሩ ከነበሩት 23 የምርምር ፕሮፖዛሎች ውስጥ ስራቸው ተጠናቆ ታህሳስ 18 እና 19 በተደረገው የምርምር ውጤቶች ማቅረብያ ቀን (Research Rreview Day) የቀረቡት 11 ሲሆኑ የተቀሩት 12 የምርምር ስራዎች በወቅቱ ስላልተጠናቀቁ ሊቀርቡ አልቻሉም። ከላይ የተገለፁት ሰፋ ያሉት ሁለት የምርምርም ስራዎች (የሂሳብ እና ሳይንስ ትምህርት ጥራት እና የፓኬጅ ፕሮግራም ውጤት) ተጠናቀው በማቅረቢያ ቀኑ ስለቀረቡ በድምሩ በ Research Rreview Day የቀረቡት የምርምር ስራዎች ብዛት 13 ነበር። በዚሁ ቀን ከመቐለ ዩኒቨርሲቲ እና በከተማው ከሚገኙ ፅ/ቤቶች ባለሞያዎች የተገኙ ሲሆን በምርምር ውጤቶቹ ላይ አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል። ጥናታቸው አልቆ ለህዝብ የቀረቡት የምርምር ፕሮፖዛሎች የሚከተሉት ናቸው፤

ሰንጠረዥ 16፤ ታሕሳስ 18 እና 19/2006 በተደረገው የምርምር ቀን አልቀው የቀረቡ ምርምሮች

| S.No. | Research Title | College | Department of Principal Inv. |
|---|---|---|---|
| 1 | Assessment on Major Health Constraints and Production System of Market Oriented Livestock Development: GantaAfeshum | CAES | Animal Prodn and Tech |
| 2 | Incidence of Poverty and Tourism Development in Tigray: Eastern Zone | CBE | Economics |
| 3 | Effect of Drought Risk Management and Coping Strategy on Welbeing of Rural Households in Tigray | CBE | Accounting and Finance |
| 4 | Impact of Controlled Grazing Technique on Livelihood of Rural Communities | CBE | Economics |
| 5 | Assessing the Performance of Urban Land Lease Policy Implementation and Practices in Tigray | CBE | Economics |
| 6 | Determinants of Quality Adulteration Effects of Honey from Adigrat and Surrounding Areas | CNCS | Chemistry |
| 7 | Challenges and Success in Implementation of Government Budget System: Case of Tigray | CSSH | Geography and Env. Studies |
| 8 | Students of SSH Reluctance to Join the Department of English: Adigrat and Axum | CSSH | Eglish |
| 9 | Contribution of Scientific Research Collaboration and | CSSH | Psychology |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | Publications for R&D in Tigray | | |
| 10 | Assessing Dimensionality and Validity of Teachers Performance Evaluation in Eastern Zone High Schools | CSSH | Psychology |
| 11 | Assessment on the Implementation of Students' Score Based Evaluation Systerm and its Impact in Tigray Schools | CSSH | English |
| 12 | Assessing the Quality of Mathematics and Science Education in Highschools of Eastern Tigray | University | |
| 13 | Impact Evaluation of the Integrated Household Package Program in Tigray | University | |

በ2006 አዲስ ምርምሮችን ለማካሄድ ደግሞ ጥሪ ቀርቦ 101 የምርምር ፕሮፖዛሎች የተዘጋጁ ሲሆን በኮሌጅ ደረጃ የመምረጥ ስራ የተከናወነ ሲሆን በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ደግሞ ዳግም የማጣራትና የመምረጥ ስራ ተከናውኖ (ከመቐለ ዩኒቨርሲቲ የመጡ ባለሞያዎችም ጭምር በመጠቀም፣ ይሄም የሆነበት ምክንያት በኮሌጅ ደረጃ በተደረገው የምርምር ፕሮፖዛሎች አመራረጥ ላይ በርከት ያሉ ቅሬታዎች ቀርበው ስለነበር ነው) 26 የምርምር ፕሮፖዛሎች ተመርጠውና ባጀት ተመድቦላቸው በመሰራት ላይ ይገኛሉ። ተመርጠው በመሰራት ላይ የሚገኙት ፕሮፖዛሎች በሚከተለው ሰንጠረዥ የተመለከቱት ናቸው።

ሰንጠረዥ 17. በ2006 የተመረጡ የምርምር ፕሮፖዛሎችና የተመደበላቸው ባጀት

| No | Research/Project proposal Title | Principal Investigator | Department | College | Approved Budget |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Developing Human resource management system for ADU | Mehari Mesfin | Computer Science & IT | CET | 49,757.40 |
| 2 | Establishment of strong linkage b/n Universities and Industries | Ayenew Yihune | civil engineering | CET | 21,075.00 |
| 3 | Production and charecterization of wine from Cactus Fruit | Zinabu Hailu | Chemical Eng. | CET | 49,756.00 |
| 4 | Preparation of a design for the main Entrance , Fence and campus prison of ADU | Brhane G/Tensay | civil engineering | CET | 40,500.00 |
| 5 | Developing Digital institutional repository for ADU | Hailay w/gebriel | Computer Science & IT | CET | 49,749.00 |
| 6 | Implementation of grouping technology and celluar manfuracturing system | Seid Muhie | Mechanical Eng. | CET | 22,907.50 |
| 7 | Opportunities and Challenges in Using Action Research as a Tool for Improving Teacher Quality and Classroom Practices: The Case of Selected Schools in Tigray. | Fiseha Gidey | Maths | CNCS | 49,702.90 |
| 8 | Quality Assessment of Local Clay Raw Materials for Pottery Products: Implication to Improve Livelihood of Potters in Eastern Tigray, Northern Ethiopia | Tadesse G/mariam | Chemistry | CNCS | 49,996.00 |
| 9 | Cactus Potential as Natural Coagulant in Water Treatment; Anticorrosion Activity on Iron Metal Sheets | Tessema Derbe | Chemistry | CNCS | 49,875.00 |
| 10 | Phytochemical and Ethno Botanical Study of Medicinal Plants Used In Ectoparasite Infections of Ruminant | Mebrahtu Hishe | Biology | CNCS | 48,939.90 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | animals in Eastern Tigray, Northern Ethiopia | | | | |
| 11 | Intestinal parasitic infections among HIV infected and Non- infected patients in Eastern Tigray, Northern Ethiopia | Dinku Senbeta | Biology | CNCS | 49,990.00 |
| 12 | Natural Pesticide from Eucalyptus Essential Oil against Cactus Pests | Yohannes W/Mariam | Chemistry | CNCS | 50,000.00 |
| 13 | Challenges and Opportunities of Business House Rental Income Taxation In Tigrai National Regional State. | Girmalem Nirea | Management | CBE | 50,000.00 |
| 14 | Factors That Affect Participation Of Households On Off-Farm Activities In Tigrai. | Mohammedawel Yesuf | Economics | CBE | 49,935.00 |
| 15 | Assessment Of Working Capital Financing The Case Of Manufacturing Micro And Small – Scale Enterprises (Mses) In Tigrai. | Amanuel Tesfay | Accounting and Finance | CBE | 49,985.25 |
| 16 | Determinants of the Socio-Economic of Family Planning in Tigrai National Regional State. | Yibrah Hagos | Economics | CBE | 50,000.00 |
| 17 | Improving Livestock Management as a Means for Enhancing Productivity and Health | Berihu H. | ANPT | AES | 50,000.00 |
| 18 | GIS Based Land Suitability Evaluation for Main Irrigated Vegetables in Semaz Dam, Northern Ethiopia. | Abraham M. | NRM | AES | 36,987.50 |
| 19 | Assessment of Modern Beehive Productivity and Its Challenges: In The Case of Eastern Zone of Tigray Region, Northern Ethiopia | Niguse G. | ANPT | CAES | 46,988.60 |
| 20 | Income Tax Assessment of Category 'C' Taxpayers in Tigray Region; the Pitfalls and the Way Forward | Muuz Abraha | Law | CSSH | 50,000.00 |
| 21 | "Explore the Land Use Land Cover Change (LULCC) through the combination of Quantitative (GIS and Satellite RS) and Qualitative methods over the period ranges from 1975 to 2011 in case of Kilite Awulalo Woreda, Eastern Zone of Tigray, Ethiopia" | Abineh Tilahun | Geography & Environmental Studies | CSSH | 49,972.00 |
| 22 | An assessment on utilization of literary texts on English text books and its effect in the development of learners' language proficiency in some selected elementary and junior schools. | Amanuel Weldemicheal | English and literature | CSSH | 50,000.00 |
| 23 | Assessing the socio-Economic and Environmental effect of flood on Adigrat town | Fikre Belay | Geography | CSSH | 49,900.00 |
| 24 | Assessing The Implementation of Modularization Approach In Adigrat, Axum, Samera,Weldiya and Mekelle Universities | Yared Niguse | English Language and Litrature | CSSH | 49,935.00 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 25 | Assessment Of Malnutrition And Associated Factors Among Under Five Children At Saesie Tsaeda Emba Wereda, Eastern Zone, Tigray, Ethiopia | G /medhin G/her | Public Health | CMHS | 49,799.00 |
| 26 | Intention To Use Modern Family Planning Methods Among Sexually Active Hiv Positive Reproductive Age Women Attending Art Clinics In Eastern Zone Of Tigray, Ethiopia | Yemane Berhane | Nursing | CMHS | 49,190.00 |
| | Total | | | | **1,214,941.05** |

በየአመቱ እንደሚደረገው ዩኒቨርሲቲው በ2006ም የተለያዩ የማህበረሰብ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ በአመቱ የተደረጉት ዋና ዋና የማህበረሰብ አገልግሎቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

(1) በክልል ደረጃ በከተማው የሚከበረው የመስቀል በአል በደማቅ ሁኔታ እንዲከበር የሩጫ ውድድር እና የፓነል ውይይት አዘጋጅቷል፡

(2) የከተማው ስፖርት ክበብ ለማጠናከር የገንዘብ እና የማቴርያል ድጋፍ ተሰጥቷል፡

(3) ከሰመራ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ለዓዲግራት ዩኒቨርሲቲ ቅርበት ያላቸው የዓፋር ክልል ወረዳዎች ማለትም ዳሉል፡ በራሕለ፡ ኮነባ፡ እና አብዓላ በትምህርት ዘርፍ ድጋፍ ለመስጠት ከወረዳ አስተዳዳሪዎች እና ከትምህርት ፅ/ቤት ሃላፊዎች ሁለት የውይይት መድረክ የተካሄደ ሲሆን በክረምት 2005 ከአንራባች የአፋር ክልል ለመጡ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች (ከትግራይ ክልል ምስራቃዊ ዞን ከመጡት ተማሪዎች ጋር) የአውትሪች ፕሮግራም ተጠቃሚ እንዲሆን ተደርጓል ፡

(4) የዓዲግራት ሆስፒታልን በህክምና መሳርያዎች ለማጠናከር ስዊድን ከሚገኘው ግብረሰናይ ድርጅት ጋር በመስማማት እና የትራንስፖርት ወጪውን በመሸፈን አራት ኮንተይነሮች ሙሉ የህክምና እቃዎች አስመጥተን ድጋፍ አድርገናል ፤ ሆስፒታሉ በነዚህ ማቴርዩሎች አመካኝነት በርካታ ችግሮችን ሊያቃልል እንደሚችል የሚታመንበት ሲሆን ከዩኒቨርሲቲው ጋር ያለው ግንኙነትም የጠበቀ እና የመደጋገፍ መንፈስ የሰፈነበት እንደሚሆን ያደርገዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከጣልያን አገር (ኤስ ኦ ከሚባል ድርጅት) ከተበረከተልን ያገለገለ አምቡላንስ ጋር የመጡ የህክምና መሳርያዎች (የኦፕሬሽን ቴብል እና ስተሪላይዘሮች) ለሆስፒታሉ አበርክተናል፤

(5) በእንግሊዝ አገር ከሚገኙ ባለሞያዎች (ዶ/ር አብርሃ ደርሶ እና ሚስ አን ደርሶ) ጋር በመተባበር አንድ ኮንተይነር ሙሉ ለዓዲግራት ሆስፒታል (እና ለዩኒቨርሲቲያችንም ጭምር) አገልግሎት የሚሰጡ የህክምና እቃዎች እና መፃህፍት እየመጡ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው የአገር ውስጥ መጓጓዣ ወጪ በመቻል (ማቴርያሎቹን የማሰባሰብና አለምአቀፍ የትራንስፖርት ወጪ በመሸፈን አገር ውስጥ እንዲገባ ያደረጉት ገባሬ ሰናይ ባለሞያዎቹ ናቸው) እየመጡልን ሲሆን እንደደረሰ ለሆስፒታሉ የሚሰጥ ይሆናል፤

(5) በዓዲግራት ከተማ ለሚገኙ ሁለት ቀበሌዎች የአከባቢ ልማት ፕላን (Local Development Plan) ዝግጅት ከከተማው አስተዳድር ጋር በመተባበር እየሰራን እንገኛለን፡፡

(6) የአትሌቲክስ ክለብ ለማቋቋም የሚያስችለን በመካከለኛ እና በረጅም ሩጫ ወጣት ስፖርተኞች መረጣ ተከናውኗል፡፡ ክለቡን በተደራጀ መልክ ለማካሄድ ዝግጅቶች እየተደረጉ ናቸው፡፡

(7) በእንግሊዝ አገር ከሚገኙ ባለሞያዎች (ዶ/ር አብርሃ ደርሶ እና ሚስ አን ደርሶ) ጋር በመተባበር አንድ ኮንተይነር ሙሉ ለዓዲግራት ሆስፒታል (እና ለዩኒቨርሲቲያችንም ጭምር) አገልግሎት የሚሰጡ የህክምና እቃዎች እና መፃህፍት መጥተዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲው የአገር ውስጥ

መጓጓዣ ወጪ በመቻል (ማቴርያሎቹን የማሰባሰብና አለምአቀፍ የትራንስፖርት ወጪ በመሸፈን አገር ውስጥ እንዲገባ ያደረጉት ገባሬ ሰናይ ባለሞያዎቹ ናቸው) በመቻል ነው ማቴርያሎቹ እና መፃህፍቶቹ የመጡት፤

(8) ከጋንታ አፈሹም ወረዳ ሃያ ቀበሌዎች የተውጣጡ 54 የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች የሁለት ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል። ስልጠናው የተሰጠው "የማህበራዎ ፍርድ ቤቶች የህግ ማእቀፍ"፤ "በቤተሰብ ህግ ስለጉዲፈቻ አተገባበር"፤ እና "ስለ ጋብቻ አመሰራረት፣ መፍረስ እንዲሁም ቀለብና ንብረት ክፍፍል" በሚሉ ርእሶች ሲሆን ስልጠናው የተካሄደው መጋቢት 11 እና 12 ነው።

(9) ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከሚደረገው ድጋፍ ጋር ተያይዞ በትግራይ ምስራቃዊ ዞን በሚገኙት ዘጠኝ ወረዳዎች የሚገኙ 18 ትምህርት ቤቶች ለ10 እና 12 ክፍል ተፈታኝ ተማሪዎች በዩኒቨርሰቲው መምህራን አመካኝነት ፈተናዎችን የመስራት ድጋፍ ተደርጎላቸዋል። ድጋፉ በሁለት ዙር የተከናወነ ሲሆን በመጀመርያው ዙር 27 መምህራን በሁለተኛው ዙር ደግሞ 37 መምህራን ተሳትፈውበታል። የተደረገው ድጋፍ በሳይንስ (ሂሳብ፣ ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪ፣ ባዮሎጂ)፤ እንግሊዝኛና ሲቪክስ ትምህርቶች ያተኮረ ነው የነበረው።

(10) 160 ለሚሆኑ የዓዲግራት ከተማ ምክር ቤት አባላት በፌደራሊዝም፤ የህግ አውጪ አካል ሃላፊነትና ተግባራት እና ሎሎችም ርእሶች በሰኔ 20 እና 21/2006 የሁለት ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል።

### 4.3. ለሴት ተማሪዎች የተደረገ ድጋፍ

1. የኢኮኖሚ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲው ድጋፍ ያደርጋል። የሚደረገው ድጋፍ የገንዘብና የቁሳቁስ ሲሆን የገንዘብ ድጋፉ በሰሚስተር አንድ መቶ ብር ለያንዳንዱ የኢኮኖሚ ችግር ያለበት ተማሪ የሚሰጥ ሲሆን በማቴርያል መልክ የሚሰጣቸወ ደግሞ ሳሙና (የልብስና የገላ)፤ እስክርቢቶ፤ ደብተር ለወንድና ሴት ተማሪዎች የሚሰጥ ሲሆን ከዚሁ በተጨማሪ ለሴት ተማሪዎች ፓንት፤ ቅባትና፤ ሞዴስ ናቸው። እነዚህ ማቴርያሎች በአመት አንድ ጊዜ የሚሰጡ ናቸው። በዚሁም መሰረት ለነባር 116 ተማሪዎች (ከነዚህ ውስጥ ሴቶች 78 ናቸው)፤ እንዲሁም ከአዲስ ተማሪዎች 171 ተማረዎች (ከነዚህ ውስጥ 84 ሴቶች) ተመርጠው የገንዘብና የማቴርያል ድጋፍ ተሰጥቷቸዋል። ስለዚህ በድምሩ ለ287 የኢኮኖሚ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲው የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል። በዩኒቨርሲቲው የኢኮኖሚ ድጋፍ እየተደረገላቸው የሚገኙ ሴት ተማሪዎች ቁጥር 162 (56%) ነው።

2. ከሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር በተገኘው የገንዘብ ድጋፍ መሰረት ለ29 ሴት ተማሪዎች (ቀደም ብለው የተመረጡ) በየወሩ 200.00 ከ2005 ጀምሮ ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል።

3. የህይወት ክህሎት ስልጠና ለ740 ሴት ተማሪዎች ለሁለት ቀናት በስርአተ ፆታ ፅ/ቤትና በዩኒቨርሲቲው መምህራን የተሰጠ ሲሆን ስልጠናው ገና ያላገኙ ሴት ተማሪዎች ደግሞ በቀጣይነት የሚሰጣቸው ይሆናል። የማሰልጠኛ ማንዋል በሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ የተዘጋጀ ሆኖ ስልጠናው የወሰዱ መምህራን ይሄንን ስልጠና ለተማሪዎቻችን እንዲሰጡዋቸው ተደርጓል።
4. አዲስ ለተመደቡ ሴት ተማሪዎች የአቀባበል ፕሮግራም እና የበለጠ ውጤት ላመጡ ነባር ሴት ተማሪዎች የሽልማት ፕሮግራም በማዘጋጀት ህዳር 19/2006 በተደረገው ዝግጅት 32 ሴት (3.75 እና ከዛም በላይ ላመጡት) ተማሪዎች ሽልማት እንዲያገኙ ተደርገዋል።
5. በትምህርት ክፍል አመዳደብ ለሴት ተማሪዎች ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ተደርጓል። በዚሁም መሰረት 25% የሚሆኑ ቦታዎች ለሴቶች ብቻ ያለውድድረ እንዲደርሳቸው ተደርጓል።
6. ሴት ተማሪዎችን ትኩረት ያደረጉ የቱቶርያል ድጋፎች በየትምህርት ክፍሉ (በስርአተ ፆታ ፅ/ቤት አስተባባሪነት) የሚሰጥ ሲሆን በአንደኛው ሰሚስተር ድጋፉ የተጠናከረ አለመኖሩ ተገምግሞ በሁለተኛው ሰሚስተር የተሻለ ስራ እየተሰራ ይገኛል።

### 4.4. የዩኒቨርሲቲው የመጀመርያ ተመራቂዎች

ዩኒቨርሲቲው በ2004 ለመጀመርያ ጊዜ ከተቀበላቸው 960 ተማሪዎች ውስጥ አብዛኛዎቹ በኢንጂነሪንግ ኮሌጅ የተመደቡ ስለሆነ (አምስት አመታት የሚወስድ በመሆኑ) ዘንድሮ መመረቅ አይችሉም። በ2004 በ13 ትምህርት ክፍሎች ከተቀበልናቸው ውስጥ ቅዳሜ ሓምሌ 12/2006 በተከናወነው ደማቅ የምረቃ ስነስርአት ላይ የተመረቁት ከቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ (በኣካውንቲንግና ፋይናንስ፣ በኔጅመንት፣ በኢኮኖሚክስ)፣ ከተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ (ባዮሎጂ፣ ኬሚስትሪ፣ ሂሳብ፣ ፊዚክስ)፣ እና ከማህበራዊ ሳይንስና ስነ ሰብ ኮሌጅ (እንግሊዝኛ፣ ስነዜጋና ስነምግባር) በድምሩ በዘጠኝ የትምህርት መስኮች ሲሆን ዩኒቨርሲቲው በድምሮ 342 ተማሪዎችን (ከነዚህ ውስጥ 215 ወይም 63% ሴቶች ናቸው) ተማሪዎችን አስመርቋል። የምረቃው ስነስረአት ተገቢ ዝግጅት የተደረገበት እና ታሪካዊነቱን በሚያጎላ መልኩ የፌደራል እና የክልል መንግስት ሃላፊዎች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሃላፊዎች፣ እና የከተማው ነዋሪዎችና የተመራቂ ተማሪዎች በተገኙበት የተከናወነ ነበር። ክቡር አቶ አባይ ወልዱ የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ፕረዚደንት የእለቱ የክብር እንግዳ በመሆን የዩኒቨርሲቲውን የመጀመርያ ተማሪዎችን በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ በሚገኘው አዳራሽ በመገኘት ተማሪዎችን መርቀዋል።

## 4.5. የ2006 የስራ አመታዊ የስራ የኣፈፃፀም ሰንጠረዥ

| ግቦች | ሊሰሩ የታቀዱ ዝርዝር ስራዎች | የስድስት ወራት አፈፃፀም ማብራርያ እና በመቶኛ ሲገለፅ | እቅዱን በመፈፀም ያጋጠሙ ችግሮች ወይም ሁኔታዎች | የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች |
|---|---|---|---|---|
| ግብ 1. ከ4000 በላይ አዲስ ተማሪዎችን ለመቀበል ኣስፈላጊ ዝግጅቶችን በማድረግ ትምህርት መጀመርና ማካሄድ | 1.1 የግንባታ ስራዎች፤ የመሰረተ ልማት ስራዎች እና ለህንፃው ኣስፈላጊ የሆኑት ፈርኒቸሮችና ሌሎች ማቴርያሎች ኣቅርቦት በተመለከተ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ | ዩኒቨርሲቲው በያዘው በርካታ ተማሪዎችን የመቀበል እቅድ የግንባታ ስራዎች እና የማቴርያሎች አቅርቦች ከ2005 ሁለተኛው መንፈቀ አመት ጀምሮ ዝግጅት ተደርጎ ክትትል እየተደረገበት ስለተሰራ ወጤታማ ሆኖ ከ4000 በላይ ተማሪዎችን ለመቀበል አስችሎናል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.2. የሁለተኛ ዙር ግንባታዎች ለ2006 ተማሪዎች ቅበላ የሚደርሱትንና የማይደርሱትን በመለየት ክትትል ማድረግ | ለተማሪዎች ቅበላ የሚደርሱት እና የማይደርሱት በመለየት አስፈላጊው ክትትል ተደርጎበታል። ችግር በታየባቸው ግንባታዎች አስፈላጊው ድጋፍ እና ክትትል በማድረግ የተሻለ አፈፃፀም እንዲኖራቸው ተደርጓል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.3. የሶስተኛ ዙር ግንባታዎችን በዋናው ግቢ እና በሁለተኛው ግቢ መጀመር እና መከታተል | የሶስተኛ ዙር ግንባታዎች በዋናው ግቢ 31 ብሎኮች ተጀምረው አብዛኛዎቹ በመጠናቀቅ ላይ የሚገኙ ስለሆነ ዩኒቨርሲቲው ለ2007 ትምህርት ዘመን 5000 ተማሪዎችን ለመቀበል እንደሚያስችለው ይታመናል። በዚህ ሪፖርት በሰንጠረዥ መልክ እንደተቀመጠው (ተጨማሪ ማብራርያ 2 ወይም Appendix 2 ሰንጠረዥ ሐ ይመልከቱ) እስከ ሰኔ 30/2006 ድረስ ያለው አፈፃፀም ላቸው አፈፃፀም 97.91% ነው። በሁለተኛው ግቢ ለመሰራት በእቅድ ተይዘው የነበሩ 12 ህንፃዎች ተለይተው የተቀመጡ ቢሆንም የቦታ ማስለቀቅ፣ ካሳ ክፍያ፣ የማስተር ፕላን፣ እና የአማካሪ መረጣ ስራዎች ስላልተጠናቀቁ ግንባታው ሊጀመር አልቻለም። ሆኖም ሁለተኛውን ግቢ የማጠር ስራ ግን በአብዛኛው ተጠናቋል (አፈፃፀም 85%) | | |
| | 1.4. በመሰራት ላይ ያሉት የመሰረተ ልማት (የውስጥ ለውስጥ | የመሰረተ ልማት ስራዎች (የውስጥ ለውስጥ መንገድ፤ የውሃ፤ የኤሌክትሪክ እና የፍሳሽ) | የትሪትመንት ፕላንት ለመስራት | ከጋንታ አፈሹም ወረዳ አስተዳደርና |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | መንገድ፤ የኤሌክትሪክ፤ የውሃና ፍሳሽ) ግንባታ መከታተል፤ የትሪትመንት ፕላንት ግንባታ መጀመርና መከታተል | ስራዎች አስፈላጊው ክትትል እየተደረገባቸው በጥሩ ሁኔታ ለተማሪዎች ቅበላ ደርሰዋል። እስከ 2005 ክረምት እንጠቀምበት የነበረው የውሃ መስመር በዲዛይኑ መሰረት የተሰራው ሳይሆን በመጠባበቅያ የእሳት ማጥፊያ መስመር ይተላለፍ ስለነበር ተፈላጊው የውሃ አቅርቦ ሊገኝ አልተቻለም ነበር። ሆኖም አዲስ ተማሪዎች በሚገቡበት ጊዜ በዲዛይኑ መሰረት መስመሩ ስለተሰራ የተሟላ የውሃ አቅርቦት ሊገኝ ችሏል። የኤሌክትሪክ አቅርቦትም በትራንፎርመር እጥረት ምክንያት ችግር የነበረበት ሲሆን በዚህ አመት ተጨማሪ 3 ትራንስፎርመሮች ተገጥመው አገልግሎት እየሰጡ ስለሆነ የተሟላ የኤሌክትሪክ አቅርቦት እየተሰጠ ይገኛል። ስለዚህ በውሃ እና በኤሌክትሪክ በኩል የነበረው ችግር ስለተፈታ (ከውሃ ጀነሬተር/ትራንፎርመር እና ከኤሌክትሪክ መቆራረጥ ጋር ተያይዘው ችግሮች አጋጥመው የነበረ ቢሆንም) በወሳኝ መልኩ በቂ አገልግሎት ሊሰጥ ተችሏል። የፍሳሽ አገልግሎት በተመለከተም በሽንት ቤቶች አከባቢ ችግሮች የነበሩ ቢሆንም በግንባታ በኩል መሻሻሎች ስለተደረጉ የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት አስችሎናል። የውስጥ ለውስጥ መንገድ የኮብልስቶን ዝርጋታም በጥሩ ሁኔታ ተጠናቆ (ጥገና የሚያስፈልጋቸው ቦታዎች ያሉ ቢሆንም) አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። የፍሳሽ ማጣርያ ፕላንት (Treatment Plant) ለማሰራት ተጨማሪ መሬት ከአከባቢው አስተዳደር ጋር በመነጋገር ስለተገኘ ከካሳ ግመታ እና ተለዋጭ መሬት ከመስጠት ጋር ተያይዞ መዘግየቶች የነበረ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ወደ ግንባታ ስራው መግባት ተችሏልል። (አፈፃፀም 90%) | ተጨማሪ መሬት ያስፈልግ ስለነበረ የካሳ ግምት ከተሰራ በኋላ ከአከባቢው መነሳት የነበረባቸው ነዋሪዎች ተለዋጭ ቦታ ሳይሰጠን አንነሳም በማለታቸው እና ያልተገመተልን ንብረት አለ የሚሉ ጥያቄዎች በመቅረባቸው በነዚህ ምክንያቶች የግንባታ ስራው በወቅቱ ሊጀመር አልቻለም። | ከከተማው ከንቲባ ፅ/ቤት በመነጋገር የተለዋጭ ቦታ ጉዳይ እንዲፈታ ተደርጎ ግንባታው እየተከናወነ ሲሆን ሊገመትልን ይገባ የነበረና ያልተገመተልን ንብረት አለ የሚሉ ጥያቄዎች ግን እስከ ፍርድ ቤት ቀረበዋል። |
| | 1.5. ለ8000 ያህል ተማሪዎች የውሃ አቅርቦት መዘጋጀቱን ማረጋገጥና መከታተል | በዲዛይኑ መሰረት የግቢው የውሃ መስመር ስለተሰራ እና በሁለቱ የውሃ ጉድጓዶች ትራንስፎርመሮች በወቅቱ ስለተገጠሙ የውሃ አቅርቦቱ አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ ተሰጥቷል። ሆኖም በአመቱ መጨረሻ አከባቢ የውሃ መጠን መቀነስ ስለታየ ለ2007 | የውሃ ትራንስፎርመር መዘግየት፤ አልፎ አልፎም የቆጣሪ ብልሽቶች | ከሚመለከታቸው ጋር በመነጋገር ችግሮቹ እንዲፈቱ ተደርገዋል። ለ2007 ደግሞ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ተጨማሪ የውሃ ጉድጓድ በማስቆፈር አቅርቦቱን ማሳደግ ያስፈልጋል (አፈፃፀም 95%) | አጋጥመዋል። የውሃ አቅርቦት መቀነስም ታይቷል። | ተጨማሪ የውሃ ጉድጓድ በማስቆፈር አቅርቦቱን ለማሳደግ እቅድ ይያዛል። |
| | 1.6. የዩኒቨርሲቲው መግቢያ (ሁለተኛው በር) ማሰራት | ወደ ዩኒቨርሲቲው የመግቢያ በር ከመሰራቱ በፊት ከዋናው መንገድ ወደ ዩኒቨርሲቲው ግቢ የሚያስገባው መንገድ በአስፋልት ለማሰራት ዝግጅቶች ተደርገው የውቅሮ ዛላአንበሳ መንገድ ሰርቶ በማጠናቀቅ ላይ ባለው የቻይና ኩባንያ አመካኝነት በጥሩ ሁኔታ ተሰርቶ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.7. ለተማሪ ቅበላ ለሚደርሱ ህንፃዎች የኤሌክትሪክ አቅርቦት መኖሩን ማረጋገጥና መከታተል | ተጨማሪ ትራንስፎርመሮችን በማስገባት አጥጋቢ የሆነ የኤሌክትሪክ አቅርቦት እንዲኖር ተደርጓል። (አፈፃፀም 100%) | የኤሌክትሪክ መቆራረጥ በተደጋጋሚ አጋጥሟል። | የመጠባበቅያ ጀነሬተር ተገዝቷል፤ አገልግሎት በከፊል ሰጥቷል። የመስመር ዝርጋታ በማድረግ የተሟላ አገልግሎት የሚሰጥ ይሆናል። |
| | 1.8. ኤሌክትሪክ በማይኖርበት ጊዜ ሊያገለግል የሚችል ጀኔሬተር እንዲገዛ ጨረታ ማውጣትና ግዥውን መከታተል | በእቅዱ መሰረት የመጠባበቅያ ጀነሬተር ግዥ ተደርጎ ተተክሏል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.9. የግቢ እና የህንጻዎች ጽዳት ክትትል ማድረግ | የፅዳት ስራ ወደ ውጭ እንዲወጣ (outsource) የተደረገ ስለሆነ በጥሩ ሆኔታ እየተሰራ ይገኛል። በ2005 ከነበሩት ህንፃዎች በተጨማሪ ሌሎች ግንባታዎች አልቀው አገልግሎት ላይ ስለዋሉ ለተጨማሪ የፅዳት ስራ ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር በማስፈቀድ በ2005 ይሰራ በነበረው ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋም አመካኝነት ተሰርቷል። ከመጋቢት 2006 ጀምሮ ደግሞ አዲስ ጨረታ ቀደም ብሎ ወጥቶ ስለነበር አሸናፊ በሆነው ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋም ስራው ተሰርቷል | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.10. ያሉት አውቶቡሶችና አስገላጊ ከሆነም ሌሎች በመከራየት ቀልጣፋ እና ግልጽ የትራንስፖርት አገልግሎት ማጠናከር እና መተግበር | ሁለት ተጨማሪ አውቶቡሶች በመከራየት አጥጋቢ የሆነ የሰርቪስ አገልግሎት ተሰጥቷል። (አፈፃፀም 100%) | የአውቶቡሶች አጥረት አጋጥሞናል | ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመነጋር ተጨማሪ አውቶቡሶችን ለመግዛት ታስቦ የነበረ ቢሆንም ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈቃድ ስላተገኘ ሊሳካ አልቻለም |
| | 1.11. የጥበቃ አገልግሎት ማጠናከር እና መተግበር | ዋናው ግቢ በጊዚያዊ አጥር ብቻ የታጠረ ስለሆነ እና ከአከባቢው እና ራቅ ካለ ገጠር ቦታዎች የሚመጡ ሰዎች ወደ ከተማ የሚመላለሱበት መንገድ ቀደም ብሎ ያልታሰበበት እና ያልተዘጋጀ በመሆኑ በዩኒቨርሲቲው ግቢ እንዳይጠቀሙ መከልከል አስቸጋሪ ሆኗል። ከዚሁም በተጨማሪ በርካታ የግንባታ ሰራተኞች ስለሚመላለሱበት የጥበቃ ስራው ከባድ እንዲሆን አድርጎታል። በአሙቱ መጨረሻ አከባቢ እንደመፍትሄ ዩኒቨርሲቲው የወሰደው እርምጃ በግቢው ዳር ዳር ከራሱ መሬት በመቀነስ ለመንገድ የሚሆን ቦታ በማዘጋጀት እና በማስጠረግ ተላላፊዎች በተዘጋጀላቸው አዲስ መንገድ እንዲጠቀሙ ለማድረግ ተችሏል። የጥበቃ ሰራተኞችም በአንድ ለአምስት ተደራጅተው ስራዎቻቸውን በየወቅቱ እየገሙ እንዲሰሩ እየተደረገ ነው። (አፈፃፀም 75%) | የእሳት ማጥፊያዎች ስርቆት አጋጥሞ ነበር፤ የኳሶች መጥፋትም አጋጥሟል። | ስርቆቱን ያከናወኑት ተማሪዎች በፖሊስ ተይዘው ጉዳያቸው ፍርድ ቤት ቀርቦ የእስር ቅጣት ተወስኖባቸዋል። ለ2007 ግቢውን የማጠር ስራ በእቅድ የሚያዝ ይሆናል። |
| | 1.12. ተማሪዎች በጥሩ ሁኔታ መቀበል የሚያስችለን የተለያዩ ፎርኒቸሮች፤ አልጋዎችና ፍራሾች በጊዜው እንዲሟሉ ማድረግ | ለተማሪዎች ቅበላ የሚሆኑ ማቴርያሎች በ2005 ጨረታ እንዲወጣ በማድረግ ተማሪዎች በሚገቡበት ጊዜ በአብዛኛው እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን የቺፕውድ አቅርቦት ግን በከፊል ለጥቂት ቀናት የዘገየበት ሁኔታ አጋጥሞ ነበር። (አፈፃፀም 90%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 1.13. የተማሪዎች ሎከሮች በትናንሾቹ ዶርሚተሪዎች በኮንትራክተሮች እንዲዘጋጁ ማድረግ | በተያዘው እቅድ መሰረት ተፈፅሟል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.14. በጠቅላላ 8000 ያህል መደበኛ ተማሪዎችን ለማስተናገድ በሚያስችለን መልኩ መምህራንና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ቅጥሮች ማከናወን ወይም በዝውውር መቅጠር | የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ቅጥር እንዲሁም የመምህራን ምደባ (በትምህርት ሚኒስቴር የተመደቡ)፤ ቅጥር እና ዝውውር ተደርጎ ከሀክምና ዶክተሮች ውጪ በቂ አቅርቦት እንዲገኝ ተደርጓል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.15 የአመቱን የትምህርት መርሃግብር ማውጣትና ማፅደቅ | የአመቱ የትምህርት መርሃ ግብር ወጥቶ በዚሁ መሰረት ተፈፅሟል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.16 ለአዲስ ተማሪዎች ኦርየንቴሽን መስጠት፤ የትምህርት ክፍል ምደባና፤ የትምህርት ፕሮግራሞች ማሳወቅ | በትምህርት ክፍል ምደባ ቅድሚያ ለሴት ተማሪዎች እንዲሰጥ ተደርጓል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.17 የአመራር አቅም መገንባት ስራዎችን ማከናወን | የአመራር አቅም ግንባታ ለማዳበር 2005 ክረምት ላይ ትምህርት ሚኒስቴር ባዘጋጀው የሁለት ሳምንት የስልጠና ፕሮግራም በየደረጃው በአካዳሚው ክንፍ የሚገኙ ሃላፊዎች የተሳተፉበት ስልጠና ተሰጥቷል። ከዚሁም በተጨማሪ በየጊዜው በእቅድ ዝግጅት እና በአፈፃፀም ያተኮሩ ውይይቶችና ግምገማዎች በማድረግ የአመራር አቅም ግንባታን የማጎልበት ስራ ተሰርቷል። (አፈፃፀም 75%) | | |
| | 1.18 የቡድን ስራ ባህልን ማበረታታት እና ማጠናከር፤ የመምህራንና የሰራተኞች የአንድ ለአምስት ቡድኖችን ማጠናከርና መከታተል | የተማሪዎች፤ የመምህራን እና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች የአንድ ለአምስት መረቦች እና የልማት ቡድኖችን ለማቋቋም የሚያስችል ማንዋል (በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀውን ማንዋል መሰረት በማድረግ) ተዘጋጅቶ በአፈፃፀሙም ላይ ውይይት ተደርጎበት ወደ ትግበራ ተገብቷል። በዚሁም መሰረት በአንደኛ ሰሚስተር በድምሩ (የተማሪዎች፤ የመምህራንና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች) 1478 ቡድኖች በማቋቋም የተሰራ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ሲሆን በሁለተኛው ሰሚስተር ደግሞ በተማሪዎች አከባቢ ብቻ 1211 የአንድ ለአምስት 136 የልማት ቡድኖች ተቋቁመው ከአንደኛ ሰሚስተር የተሻለ አፈፃፀም ለማስመዝገብ ተችሏል። በአጠቃላይ ሲታይ በዩኒቨርሲቲው የትምህርት ልማት ሰራዊት ለመገንባት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል። (አፈፃፀም 90%) | | |
| | 1.19 በየደረጃው ለሚገኝ አመራር እውቀቱ ክህሎቱና አመለካከቱ በልምድ ልውውጥ እና በስልጠና ማሳደግ | የልምድ ልውውጦች በየክፍሉ የሚደረጉ ሲሆን ስልጠናዎችም በዋናነት በሌሎች መስሪያቤቶች ጋባዥነት ተደርገዋል። (አፈፃፀም 70%) | | |
| | 1.20 ከሙስና ነጻ የሆነ እና በመልካም ስነ-ምግባር የተካነ አመራር መፍጠር፤ የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ፅ/ቤት ማደራጀት | የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ፅ/ቤት ሃላፊ ቅጥር ተካሂደዋል። የውስጥ አሰራር መመርያዎች ተዘጋጅተው ጥቅም ላይ እየዋሉ ናቸው። የዩኒቨርሲቲው ስራ ከፌደራል ዋና ኦዲት በመጡ ባለሞያዎች ኦዲት ተደርጎ በኦዲት ግኝቶች ላይ የማውጫ ኮንፈረንስ ተደርጎበታል። በውስጥ ኦዲት በተደረገው የሰው ሃብት ቅጥር እና ደረጃ እድገት፤ በመኪኖች አጠቃቀምና ስምሪት፤ እንዲሁም የፋይናንስ ኦዲትም የማውጫ ኮንፈረንስ ተደርጎበታል። በቀረቡት ግኝቶች አመካኝነት የማስተካከያ እርምጃዎች የተወሰዱ ቢሆንም ግብረ መልስ አሰጣጥ ላይ መዘግየቶች ታይተዋል። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | 1.21 መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞች ከአገር ውስጥም ከውጭ አገርም (ከህንድና ከፊሊፒንስ) መቅጠር፤ | ከህንድ አገር 11 አዲስ መምህራን ተቀጥረዋል። ከፊሊፒንስ ለመቅጠር የተደረገው ሙከራ ግን የተሳካ አልነበረም (የተመረጡት ባለሞያዎች ሊመጡ አልቻሉም)። (አፈፃፀም 95%) | | |
| | 1.22 የተጠናከረ የማባዣ ክፍል በማደራጀት ከነባር ዩኒቨርሲቲዎች የሚገኙትን መፃህፍትና የማስተማርያ ማቴርያሎች ማዘጋጀትና ማቅረብ፡ መፃህፍትን በሶፍት ኮፒ ማሰባሰብ | ከነበሩን የማባዧ መሳርያዎች በተጨማሪ አዲሶችን በመግዛት ጥሩ አገልግሎት ተሰጥቷል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.23 ወደውጭ እንዲወጣ (outsource) የተደረገው የፅዳት | ተጨማሪ ህንፃዎችም ጭምር በሚያካትት መልኩ አውትሶርስ የማድረግ ስራው በተሳካ ሁኔታ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ስራን መከታተል፤ ሌሎች መውጣት ያለባቸውም በጥናት መለየትና ማስፈፀም | ተከናውኗል። ሌሎችን ወደ ውጭ ለማውጣት (ለምሳሌ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ) ታስቦ የነበረ ቢሆንም አልተፈፀመም (አፈፃፀም 75%) | | |
| | 1.24 የተከላ ቀን በመወሰን የዩኒቨሲቲው ህብረተሰብ በስፋት የሚሳተፍበትና በባለሞያዎች የተደገፈ ተክሎችን የመትከል ስራ ማከናወን | ሐምሌ ወር 2005 ላይ ተከናውኗል። ከ20ሺ በላይ ችግኞች ተተክለዋል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.25 ለመምህራን መኖርያ የሚሆኑ ያላለቁ ኮንደሚንየም ቤቶች ግዥ ማከናወን | 12 ያላለቁ ኮንደሚንየም ቤቶች በ21 ሚልዮን ብር ከክልሉ የቤቶች ልማት ኤጀንሲ ተገዝተዋል። የተከዙት 12 ብሎኮች ሲሆኑ ርክክብ ስራው ለመፈፀም ኮሚቴ የተቋቋመ ቢሆንም ርክክቡ ገና አልተፈፀመም (አፈፃፀም 75%) | | |
| | 1.26 የመጀመርያ ምረቃ ለማካሄድ ዝግጅቶችን ማድረግ (የጋዋን ግዥዎች ማድረግ) እና በደመቀ ሁኔታ ማክበር | የጋዋን ግዥ ጨረታ ወጥቶ አሸናፊ ተለይቶ ውል ታስሮ የሪበን መረጣ (በየኮሌጁ) ተደርጎ ስራው ተከናውናል። ሆኖም በማስተርስ ደረጃ እና በፒኤችዲ ደረጃ የሚያስፈልጉት ስላልተሟሉ ከመቐለ ዩኒቨርሲቲ በመበደር እንዲሟሉ ተደርጎ ምረቃው ተከናውኗል። (አፈፃፀም 90%) | | |
| | 1.27 ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመርጠው ለሚመጡ (ከምስራቃዊ ዞን እና ከአፋር አጎራባች ወረዳዎች) ተማሪዎች የክረምት የአውትሪች ፕሮግራም ማከናወን | ከክልሉ የትምህርት ቢሮ ጋር በመተባበር በክረምት አውትሪች ፕሮግራም 207 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ከትግራይ ክልል ምስራቃዊ ዞን እና ከአጎራባች የአፋር ወረዳዎች) የተውጣጡ ተጠቃሚ ሆነዋል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.28 የክረምት ትምህርት መጀመር (Technical drawing, business education, information technology, and nursing) | ከትምህርት ሚኒስቴር በተመደቡልን፤ ከክልሉ የጤና ቢሮ ጋር በተደረገው ስምምነት፤ እና የግል አመልካቾችና በማካተት ለ403 የክረምት ተማሪዎች በአራት ፕሮግራሞች (ቴክኒካል ድረዊንግ፤ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፤ ነርሲንግ፤ እና ማኔጅመንት) የክረምት ትምህርት 2005 ክረምት ላይ ጀምረናል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.29 በዶርሚተሪዎች አከባቢ የመድሃኒት መርጨት ስራዎችን | ለክረምት እረፍት ተማሪዎች ዶርሚተሪዎችን ለቀው በሄዱበት ወቅት የመድሃኒት ርጭት | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ማከናወን፤ የክረምት ጥገና ስራዎችን ማከናወን | ተከናውኗል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 1.30 የካይዘን ስልጠናዎች መስጠትና በተፈላጊ ቦታዎች መተግበር | የካይዘን ጥናት ተደርጎ ካይዘን የሚፈለግባቸው የዩኒቨርሲቲው ክፍሎች ተለይተዋል። ስልጠናው ደግሞ ከክልሉ ቴክኒክና ሞያ ቢሮ በተገኙ ባለሞያዎች እንዲሰጥ ተደርጎ የተግባር ስራዎችም እየተሰሩ ነው። አፈፃፀም (80%) | | |
| ግብ 2. ተቋማዊ መልካም ኣስተዳደርን ማስፈንና ማስጠበቅ | 2.1 የዩኒቨርሲቲው ኣመታዊ እቅድ ማዘጋጀትና በኣመታዊ ዝርዝር እቅዱ መወያየትና መግባባት መፍጠር | በዝግጅት ምእራፍ ላይ አመታዊ ዝርዝር እቅዱ ተዘጋጅቶ መላው የዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ በተገኘበት ውይይት ተደርጎበት መግባባት ተደርሶበት ወደ ትግበራ ምእራፍ ሽግግር ተደርጓል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 2.2. የዩኒቨርሲውን እቅድ መሰረት በማድረገ የተለያዩ የዩኒቨርሲቲው ክፍሎች የየራሳቸውን እቅድ እንዲያወጡና ከክፍሎቻቸው ሰራተኞች ጋር እንዲወያዩባቸው ማድረግ | የተለያዩ የዩኒቨርሲቲ ክፍሎች ከዋናው እቅድ ጋር በማስማማት ዝርዝር እቅዶቻቸውን አውጥተው ከየክፍሎቻቸው ጋር ውይይት አድርገውበታል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 2.3. የመንግስት መመርያዎችን መሰረት ያደረገ የሃብት አስተዳደር ስርዓት መተግበር | | | |
| | • ቀልጣፋ እና ወጪ ቆጣቢ የሃብት አጠቃቀም ስርዓት ማጠናከር | ግዥዎች በወቅቱ ለማካሄድ ያስችለን ዘንድ አዲስ ተማሪዎችን ለመቀበል የሚያስፈልጉት ማቴርያሎች ግዥ ለማካሄድ በ2005 መጨረሻ አከባቢ አንድ ግልፅ ጨረታ እንዲወጣ ተደርጓል። ሌሎች ተጨማሪ ሁለት ግልፅ ጨረታዎችም ወጥተው ግዥዎች እየተካሄዱ ነው። ከመመርያው ወጣ ያሉት ግዥዎች ሲያጋጥሙ ደግሞ ከመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ፈቃድ እየተጠየቀ እንዲፈፀም ተደርጓል። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | • የግዥ አፈፃፀሙ በዕቅድ የተመሰረተ፣ ከሙስና የፀዳ፣ ወቅታዊ ቁጥጥር ያለበት እና መልካም ገጽታ የሰፈነበት ማድረግ | የግዥ ስርአቱ በእቅድ እንዲመራ ያስችል ዘንድ አመታዊ የግዥ ፍላጎት በየክፍሉ ከተዘጋጀ በኋላ በዩኒቨርሰቲ ደረጃ በግዥ ክፍሉ እንዲጠቃለል ተደርጓል። በግዥዎች ላይ ቅሬታዎች ሲያጋጥሙ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | እየታዩ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | • የገበያ ጥናትን መሰረት በማድረግ በሚፈለገው ጊዜ፣ ጥራት እና መጠን ግዥ መፈጸም | ግዥዎች በገበያ ጥናት እየታገዙ ነው የሚፈፀሙት። የገበያ ጥናት የሚያካሂድ ክፍል በግዥና ንብረት አስተዳደር ስር ተደራጅቶ ጥናቶችን ያቀርባል። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | • የውስጥ ኦዲት ስርዓት ማጠናከር እና መተግበር | የውስጥ ኦዲት ስራዎች በአግባቡ የሚካሄዱ ሲሆን የኦዲት ክፍሉ በሰው ሃይል ለማጠናከር ቅጥር ለማካሄድ ማስታወቅያ የወጣ ቢሆንም በተፈላጊ ተወዳዳሪዎች እጥረት ምክንያት ሊሳካ ስላተቻለ እና አንድ ሰራተኛም ስለለቀቀ የታቀዱስ ስራዎችን በተሟላ ሁኔታ ማከናወን አልተቻለም። (አፈፃፀም 80%) | | |
| | • ግልጽ የንብረት ስርጭት እና አጠቃቀም ስርዓት ማበጀት እና መተግበር | ንብረት ሲገዛ በፈላጊው አካል ወይም በሚመለከተው ሃላፊ ጠያቂነት እና አፅዳቂነት ሲሆን ንብረት ገቢ ከመሆኑ በፊት በቴክኒክ ኮሚቴ እንዲፈተሽ ይደረጋል። የሚመለከተው ክፍል ደግሞ ንብረቱ እንዲደርሰው ይደረጋል። (አፈፃፀም 90%) | | |
| | • የንብረት ቆጠራ በወቅቱ ማካሄድ እና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማቅረብ | የ2005 ንብረት ቆጠራ የተካሄደ ቢሆንም አላስፈላጊ መዘግየት ታይቶበታል፤ የ2006 የንብረት ሪፖርቶች ግን በየወሩ እንዲቀርቡ እየተደረገ ነው። (አፈፃፀም 70%) | | |
| | • በግልፅ ጨረታ በዓመት ሁለት ጊዜ ግዥ መፈጸም፤ እንደአስፈላጊነቱ የለቀማ ግዥዎችን በማስፈቀድ መፈፀም | በአመቱ ውስጥ አምስት ጨረታዎች ተከናውነዋል። ከግልፅ ጨረታዎቹ በተጨማሪም የውሱን ጨረታ፤ የፕሮፎርማ፤ እና የቀጥታ ግዥዎች ተደርገዋል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | • የፋይናንስ አስተዳደር ሶፍትዌር ተግባር ላይ እንዲውል ማድረግ | አይቤክስ የተባለው የፋይናንስ ሶፍትዌር በተግባር ላይ ውሏል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | • የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት በየወሩ ለዩኒቨርሲቲው ሃላፊዎች እንዲደርስ ማድረግ ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ደግሞ በህጉ መሰረት | ሪፖርቶች በወቅቱ ይደርሳሉ፤ ለሚመለከታቸው ፅ/ቤቶች ይላካሉ። የውስጥ ገቢ ሪፖርትም በ2005 ያልተሰራ ቢሆንም በ2006 መጀመርያ ላይ ተሰርቶ ተልኳል። (አፈፃፀም 90%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ለሚመለከታቸው አካላት እንዲቀርብ ማድረግ (የመደበኛ የካፒታልና የውስጥ ገቢ) | | | |
| | • የ2007 ባጀት የፕሮግራም በጀት አዘገጃጀት መሰረት በማድረግ ማዘጋጀት | የ2007 ባጀት በወቅቱ ተዘጋጅቶ ወደሚመለከተው ክፍል ተልኳ። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 2.4 በቀልጣፋ እርምጃ (QUICK WINS) መሰራት ያለባቸውን በመለየት እቅድ በማውጣት መፈፀም | በቀልጣፋ እርምጃ የሚሰሩት ተለይተው ግኙዎች እየተደረጉ ቢሆንም የአፈፃፀም መዘግየት ታይቶባቸዋል። (አፈፃፀም 65%) | | |
| | 2.5. የሰኔት ለጂስሌሽን ማስፀደቅና መተግበር። የተዘጋጁት የውስጥ መመርያዎችን መተግበር፤ ያልተዘጋጁት ደግሞ እንዲዘጋጁ ማድረግ | የሰኔት ለጂስሌሽን በሰኔት ፀድቋል። ጥቅም ላይ ከዋሉት የውስጥ መመርያዎች በተጨማሪ የሰራተኞች የደንብ ልብስ እና ሌሎች ማቴርያሎች አሰጣጥ መመርያ ተዘጋጅቶ ፀድቆ ተግባር ላይ እየዋለ ይገኛል። (አፈፃፀም 90%) | የአደጋ ትንተና መመርያ አልተዘጋጀም | |
| | 2.6 በየሩብ ኣመቱ ሪፖርቶችን ማዘጋጀትና በሪፖርቶቹ ውይይቶችን ማካሂድ | በየሩብ አመቱ ሪፖርቶች እየተዘጋጁ ለእቅድና ተቋማዊ ለውጥ ፅ/ቤት ይላካሉ። በየደረጃው ውይይት ይደረግባቸዋል። ለምሳሌ የስድስት ወር የአጠቃላይ የሰራተኞች ግምገማ ጥር 21/2006 ላይ ተደርጓል። ከዚሁም በተጨማሪ ከመምህራን ጋር ሁለት ተጨማሪ መድረኮች ተዘጋጅተው የመግባባት ስራዎች ተሰርተዋል(አፈፃፀም 100%) | | |
| | • የዩኒቨርሲቲው ኣስተዳደር ካውንስል በየሁለት ሳምንቱ ኣንድ ጊዜ እየተገናኘ ኣፈፃፀሞችንና ሂደቶችን መከታተል | አስተዳደር ካውንስሉ በየጊዜው እየተገናኘ ውሳኔዎችን ያሳልፋል፤ ስራዎችን ይገመግማል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | • የዩኒቨርሲቲው ሰኔት በወር ኣንድ ጊዜ እየተገናኘ ክትትሎችን ማድረግና ውሳኔዎችን ማሳለፍ | በአመቱ ውስጥ በርካታ የሰኔት ስብሰባዎች የተደረጉ ሲሆን ከዚሁ በተጨማሪም ደግሞ አራት የዩኒቨርሲቲ ካውንስል ስብሰባዎች ተደርገዋል ። (አፈፃፀም 95%) | | |
| | • የኣካዳሚክ ምክትል ፕረዚዳንት፤ የኮሌጅ ዲኖች ፤ ረጂስትራርና የተማሪዎች ዲን በየሁለት ሳምንት ኣንድ ጊዜ | በየጊዜው እየተገናኙ ውሳኔዎችን ያስተላልፋሉ፤ ግምገማዎችን ያደርጋሉ። (አፈፃፀም 100%) | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በመደበኛነት እየተገናኙ ክትትሎችና ምክክሮች ማካሄድ | | | |
| | • የድጋፍ ሰጪ ምክትል ፕረዚደንትና በስሩ የሚገኙ ሃላፊዎች /ዳይሬክተሮች/ በየሁለት ሳምንቱ እየተገናኙ ክትትሎችና ምክክሮች ማድረግ | በየጊዜው እየተገናኙ ውሳኔዎችን ያስተላልፋሉ፤ ግምገማዎችን ያደርጋሉ። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | • የኮሌጅና የትምህርት ክፍል /ሁሉም የትምህርት ክፍሉ መምህራን የሚገኙበት/ ካውንስሎች በየሁለት ሳምንቱ አንድ ጊዜ በመደበኛነት እየተገናኙ ክትትል ማድረግና ውሳኔዎችን ማሳለፍ | በአብዛኛው የተከናወነ ቢሆንም ከኮሌጅ ኮሌጅ ከትምህርት ክፍል ትምህርት ክፍል ልዩነት ይታይበታል። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | 2.7. BSCን መሰረት ያደረገ የዩኒቨርሲው የአምስት አመት ስትራቴጂክ ፕላን ማዘጋጀት | የስትራቴጂክ እቅዱ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ (Corporate Strategic Plan) የዩኒቨርሰቲ አመራር አባላት አስተያየት ተሰጥቶበታል፤ የመጨረሻው ቅጂ በቅርቡ ይወጣል ተብሎ ይጠበቃል። የካስኬዲንግ ስራዎች ግን በ2007 የሚሰራ ይሆናል። (አፈፃፀም 65%) | | |
| | 2.8 የእቅድ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ በየጊዜው ማድረግ (ሁሉም መምህራንና ሰራተኞች የሚሳተፉበት የስድስተ ወር እና የአመቱ ማጠቃለያ ግምገማ ማከናወን) | የስድስት ወር ግምገማ ጥር 21/2006 ተደርጓል። የአመቱ መጨረሻ ግምገማ ደግሞ ሴኔ 28/2006 ተደርጓል። ከዚሁም በተጨማሪ ከመምህራን ጋር ሁለት ተጨማሪ መድረኮችን በመፍጠር በእቅዶቻችን አፈፃፀም እና በሚነሱ ጥያዎች ዙርያ ውይይት ተደርጎባቸዋል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | 2.9 ለሴቶች እና ሌሎች ልዩ ፍላጎት የሚስፈልጋቸው አካላት ድጋፍ መስጠት | | | |
| | • በውጤታቸው የላቁትን ሴት ተማሪዎች ሽልማት መስጠት | ህዳር 19/2006 የተሻለ ውጤት ያመጡ ሴት ተማሪዎች (ማለትም ውጤታቸው 3.75 እና ከዛ በላይ የሆነ) ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | • በሴቶች እና በሌሎች ድጋፍ የሚስፈልጋቸው አካላት | ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (ለምሳሌ ቤተሰብ መምህርያ፤ ማሪ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ዙርያ ከሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በትብብር መስራት | ስቶፕስ፤ የከተማው ጤና ፅ/ቤት፤ ወዘተ) የትብብር ስራዎች ይሰራሉ። ከክልሉ ሴቶች ጉዳይ ቢሮም እንዲሁ (አፈፃፀም 85%) | | |
| | • የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸው የሴት እና ወንድ ተማሪዎች መደገፍ | ለ116 ነባር ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው የገንዘብና የማቴርያል ድጋፍ ተደርጎላቸዋል። ከዚሁም በተጨማሪ 171 የአንደኛ አመት ተማሪዎች ተለይተው ድጋፍ እንዲሰጣቸው በዝግጅት ላይ ይገኛል። በድምሩ ዩኒቨርሲቲው ለ287 የኢኮኖሚ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች (ከዚህ ውስጥ 162 ወይም 56% ሴት ተማሪዎች ናቸው) ድጋፍ እያደረገ ይገኛል። ከዚሁም በተጨማሪ ለ29 ሴት ተማሪዎች ከሴቶች፤ ወጣቶች እና ህፃናት በተገኘ ድጋፍ በየወሩ ብር 200.00 ድጋፍ ተደርጎላቸዋል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| | • በጸረ-ፆታዊ ትንኮሳ ፖሊሲ ዙርያ እና በስነ-ጾታ ጉዳይ በተቋሙ ማህበረሰብ በኩል ግንዛቤ መፍጠር | ዩኒቨርሲቲው የፀረ-ፆታዊ ትንኮሳ መመርያ ያዘጋጀ ሲሆን የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ (ተማሪዎች፤ መምህራን፤ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች) እንዲያውቁትና እንዲያከብሩት ጥረቶች ተደርገዋል። (አፈፃፀም 90%) | | |
| | • ፆታዊ ትንኮሳዎች ሲፈፀሙ በመከታተል ተቋማዊ/ህጋዊ መፍትሔ እንዲያገኙ ማድረግ | አስፈላጊው ክትትል ይደረጋል። በአመቱ ፆታዊ ትንኮሳን በተመለከተ የቀረቡ ጉልህ ችግሮች አልታዩም። (አፈፃፀም 95%) | | |
| | • ተማሪዎች ስለ ስነ-ተዋልዶ ጤና አጠባበቅ እና ኤች አይ ቪ/ኤድስ ግንዛቤ የማስጨበጥ ተግባር መፈጸም | ከህይወት ክህሎት ስልጠና ጋር እየተሰጠ ይገኛል። የዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ክሊኒክም የኮንደም አቅርቦት በነፃ ይሰጣል። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | 2.10 ሰላማዊ መማር ማስተማር ለማስፈን የተማሪዎች የምግብ፣ መኝታ እና ጤና አገልግሎት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ | | | |
| | • የተማሪዎች ካፊቴሪያ ብቁ እና አስተማማኝ መሆኑን ማረጋገጥ | አስፈላጊው ዝግጅቶች ተደርገው በአግባቡ ክትትል ስለሚደረግበት የተማሪዎች ምግብ ቤት አገልግሎት በጥሩ ሁኔታ እየተሰጠ ይገኛል። የምግብ ቤት ሰራተኞቹ በአንድ ለአምስት ቡድኖች ተደራጅተው በተቀናጀ ሁኔታ አገልግሎት ስለሚሰጡ ጉድለቶች ሲያጋጥሙ በፍጥነት ለማረም ምቹ ሁኔታ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ተፈጥሯል። (አፈፃፀም 95%) | | |
| | • የተማሪዎች መኝታ ክፍሎች እና አከባቢው ጽዱ እና ምቹ ማድረግ | የፅዳት ስራው አውትሶርስ በተደረገለት የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋም በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ ይገኛል። በተማሪዎች ሽንት ቤት አከባቢ ችግሮች የሚያጋጥሙ ቢኖንም የተሻለ የውሃ አቅርቦት በመኖሩ ምክንያት ችግሮቹ ከቁጥጥር የወጡ አይደሉም። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | • የተማሪዎች የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃን ከፍ ማድረግ። የክሊኒክ አገልግሎት አዲስ በተሰራው ህንፃ ማካሄድ | በ2006 የተማሪዎች ህክምና አገልግሎት ለዚሁ ተብሎ በተሰራው አዲስ ህንፃ እየተካሄደ ይገኛል። በቂ የመድሃኒት አቅርቦት እንዲኖር በመደረጉ እና የ24 ሰአት አገልግሎት እየተሰጠ ስለሚገኝ የተሻለ ውጤት ተገኝቶበታል። (አፈፃፀም 90%) | | |
| | • ተማሪዎች በምግብ በጀት አጠቃቀም ሰፋት ያለው ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ | ተማሪዎች በካውንስላቸው አመካኝነት ጥሩ ተሳትፎ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። (አፈፃፀም 95%) | | |
| | • በቂ ውሃ፣ ምግብ እና ሌሎች ለተማሪ የሚሆኑ ግብአቶች መኖራቸው ማረጋገጥ | የተቀመጡት አገልግሎቶች መጓደል እንዳይኖር ጥብቅ ክትትል ይደረጋል። ችግሮች ሲያጋጥሙ በተቻለ ፍጥነት እንዲፈቱ ይደረጋል። (አፈፃፀም 95%) | | |
| | • የተማሪዎች የስነ-ልቦና ልማት፣ በስነ-ተዋልዶ ጤና፣ በኤች አይ ቪ/ ኤድስ እና ተጓዳኝ ጉዳዮች ዙሪያ ግንዛቤ ለማሳደግ የሚያስችል ዝግጅት ማድረግ እና መተግበር | የኑሮ ክህሎት ስልጠና ተሰጥቷል። (አፈፃፀም 95%) | | |
| | • የተማሪዎች የዲሲፒሊን ሁኔታ መከታተል እና የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ | ተማሪዎች የዲሲፕሊን መመርያው እንዲያውቁት ተደርጎ ጉድለት በሚያሳዩ ተማሪዎች ደግሞ መመርያው መሰረት ቅጣቶች ይወሰዳሉ። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | • የተማሪዎች ስፖርት እና መዝናኛ አገልግሎት በሰው ሃይል እና ቁሳቁስ ማሟላት እና አገልግሎት መስጠት | በተሟላ ሁኔታ እየተሰጠ አይደለም። የስፖርት ሜዳዎች ዝግጅት እየተጠናቀቀ የሚገኝ ቢሆንም አገልግሎት ላይ ገና ስላልዋለ ጊዜያዊ አገልግሎቶች ተሰርተው ተማሪዎች እየተጠቀሙበት ነው። የጂም እቃዎች ተገዝተው እና ለዚህ የሚሆን ህንፃ ተመድቦ ለአገልግሎት ዝግጁ ሆናል። (አፈፃፀም 65%) | የተማሪዎች ላውንጅ ለመስራት የያዘው ኮንትራክተር በወቅቱ ሊያጠናቅቀው አለመቻል። የስፖርት ሜዳውም | ተማሪዎች በሰራተኞች ላውንጅ እንዲጠቀሙ ጨረታ ወጥቶ አሸናፊዎች ተለይተው ሁለት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | እየተሰራ ስለሆነ ገና ለአገልግሎት አልደረሰም። | ላውንጆች አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። |
| | • የተቋቋሙ የተማሪ ክለቦች ማጠናከር አዳዲሶች እንዲቋቋሙ ማበረታት እና እገዛ መስጠት | የተማሪ ዲሲፕሊን፤ የቻሪቲ፤ የስነፅሁፍ፤ የአረንጓዴ ክበቦች እና የሰላም ፎረም ተቋቁመው እዩሰሩ ሲሆን በተለይ የስነ ፅሁፍ ክበብ በየወቅቱ አዝናኝ የሆኑ ዝግጅቶችን እያቀረበ ይገኛል። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | • ተማሪዎች የዲሲፕሊን መመሪያውን በተገቢው እንዲያውቁት ማድረግ | ተከናውኗል። (አፈፃፀም 80%) | | |
| | • ሁሉም ያሳተፈ የተማሪዎች የእርስበርስ ግንኙነት እና ህብረ ብሄራዊነትን የሚያጠናክሩ በአሎችና ዝግጅቶች ማድረግ | የብሄር ብሄረሰቦች በአል በድምቀት እንዲከበር ተደርጓል።ለአዲስ ተማሪዎች ደግሞ የከተማው አስተዳደር፤ የከተማው ህብረተሰብ ክፍሎች፤ እና የሃይማኖት መሪዎች በተገኙበት በደማቅ ሁኔታ አቀባበል ተደርጎላቸዋል። የብሄር ብሄረሰቦች፤ የግንቦት ሃያ እና ሌሎች በአሎችም በጥሩ ሁኔታ ተከብረዋል። (አፈፃፀም 90%) | | |
| | • የተማሪዎች አንድ ለአምስት መረቦች (COOPERATIVE LEARNING) ማስፋፋት መደገፍና ማጠናከር | 1211 የተማሪ cooperative learning ቲሞች ተመስርተው ከመምህራን ደግሞ የክፍል ደጋፊዎች (mentor) እንዲመደቡ ተደርገዋል። የአንደኛ ሰሚስተር አፈፃፀም ተገምግሞ ችግሮች በአግባቡ ተለይተው በሁለተኛ ሰሚስተር የበለጠ ትኩረት ተሰጥቶት ስለተሰራበት ውጤት ተገኝቶበታል። (አፈፃፀም 90%) | | |
| | 2.11 ከባለድርሻ አካላት ግንኙነት ማስፋትና ማጠናከር | | | |
| | • የተጠናከረ የህዝብና ዓለም አቀፍ ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ | የህዝብና አለም አቀፍ ግንኙነት ፅ/ቤት ተጠባባቂ ሃላፊ ከመምህራን እንዲመደብለት ተደርጓል። (አፈፃፀም 90%) | | |
| | • የተቋሙ ነባራዊ ገጽታን በቴሌቪዥን በሬድዮና በፕሪንት ሚድያ ማስተዋወቅ | የተለያዩ አጋጣሚዎችን በመጠቀም ዩኒቨርሲቲው በተለያዩ ሚድያዎች ለማስተዋወቅ ተችሏል። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | • ከአካባቢያዊ ተቋማት ጋር | በዩኒቨርሰቲው አከባቢ ከሚገኙ ተቋማት (የዞን | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ግንኙነት ማጠናከር | አስተዳደር፤ የከተማ አስተዳደር፤ የወረዳ አስተዳደር፤ ትምህርት ቤቶች፤ ባንኮች፤ ኢንዱስትሪዎች፤ ማህበራት፤ ወዘተ) በርካታ ግንኙነቶች ተደርገዋል ። (አፈፃፀም 80%) | | |
| | • አለም አቀፍ ግንኙነቶችን ማፈላግና ማጠናከር | የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል። ከተደረጉ ጥረቶች ለመጥቀስ ያህል የቦርድ አባላት እና የዩኒቨርሲቲው ፕረዚደንት ያሉበት ቡድን በአሜሪካን አገር ተገኝቶ በርካታ ዩኒቨርሲቲዎችን ጎብኝቷል። የዩኒቨርሲቲ ፕረዚደንትና ምክትል ፕረዚደንት ደግሞ ጣልያን አገር ከሚገኙ ሁለት ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የትብብር ስምምነት ውል ተፈራርመዋል። (አፈፃፀም 80%) | | |
| | 2.12 የመንግስት ፖሊሲዎችና አሰራሮች መሰረት ያደረጉ ስልጠናዎች ማዘጋጀትና አሳታፊ ስርአት መዘርጋት | | | |
| | • በመንግስት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እንዲሁም አዋጆች ላይ ለዩኒቨርሲቲ ሰራተኞች የግንዛቤ ት/ት መስጠት | ትምህርት ሚኒስቴር ክረምት 2005 ለሶስት ሳምንታት ባዘጋጀው የአመራር ስልጠና በአካዳሚክ አመራር ዙርያ ያሉት በሙሉ እንዲሰለጥኑ ተደርጓል። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | • አሳታፊ የሆነ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት ማጠናከር | በየደረጃው ያለው አወቃቀር አሳታፊ በሆነ መልኩ እየተሰራበተ ይገኛል። ተማሪዎችም በሁሉም እርከኖች እንዲሳተፉ ይደረጋል። (አፈፃፀም 95%) | | |
| | • በተለያየ ሁኔታ የሚነሱ ቅሬታዎች በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አመካኝነት እንዲስተናገዱ ማድረግ | የአስተዳደር ሰራተኞችን በተመለከተ ቅሬታዎች በሚነሱበት ጊዜ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው የሚያየው ሲሆን በመምህራን ለተነሱት ጥያቄዎች ደግሞ አንድ ለዚሁ ተብሎ ከመምህራን ማህበር ጋር የተዘጋጀ መድረክ ስለነበር በዚሁ መልክ እንዲታይ ተደርጓ። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | • የዩኒቨርሲቲውን መምህራንና ሰራተኞች በመላ የሚሳተፉበት በአመት ሁለት ግዜ ግምገማ ማድረግ | የስድስት ወር (ጥር 21) እና የአመት ግምገማ (ሰኔ 28) በእቅዱ መሰረት ተደርጓል። (አፈፃፀም 70%) | | |
| | • የመምህራን ማህበር እንዲቋቋም ድጋፍ ማድረግ | በዩኒቨርሲቲው መምህራን ማህበር ተቋቁሟል። ይኒቨርሲቲው ድጋፍ አድርጎለታል። (አፈፃፀም | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በተቋማዊ እና ሃገራዊ ግንባታ ላይ አወንታዊ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ድጋፍ ማድረግ | 70%) | | |
| ግብ 3. የመምህራን ልማት ማጠናከር | 3.1 የመምህራን ልማት ፕላን በስትራቴክ ፕላኑ እንዲካተት ማድረግ | | | |
| | • የመጀመርያ ዲግሪ እና የሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን ለከፍተኛ ት/ት መላክ | በድምሩ 62 መምህራን (ከነዚህም 8 ውጭ አገር) ለሁለተኛ እና ለሶስተኛ ዲግሪ ትምህርት ሄደው እየተከታተሉ ይገኛሉ። (አፈፃፀም 85%) | | |
| | • በትምህርት ላይ የሚገኙትን መምህራን የት/ት ሁኔታ መከታተል | ክትትል እየተደረገ ነው። (አፈፃፀም 75%) | | |
| | • መምህራን የከፍተኛ ዲፕሎማ ፕሮግራም እንዲከታተሉ ማድረግ | አልተከናወነም። (አፈፃፀም 0%) | | |
| | • መምህራን በፔዳጎጂ እና በተማሪ ተኮር የማስተማር ስነ-ዘዴ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና እንዲሰጥ ማድረግ(ለአዳዲስ መምህራን የኢንዳክሽን ስልጠና መስጠት) | ተከናውኗል። ለአዲስ መምህራን የኢንዳክሽን ስልጠና ከመቐለ ዩኒቨርሲቲ በመጡ ባለሞያዎች የተሰጠ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ በትምህርት ጥራት እና ተገቢነት ዙርያ የከፍተኛ ትምህርት ተገቢነትና ጥራት ባለስልጣን ዳይሬክተር ዶ/ር ተስፋዬ በተገኙበት ስልጠና ተሰጥቷል። (አፈፃፀም 100%) | | |
| ግብ 4. ብቁ የአካዳሚክ ፕሮግራሞችና ስርአተ ትምህርቶች ማረጋገጥና መተግበር፤ | 4.2 ተከታታይ ምዘና /Continuous Assessment/ እና መስፈርት ወይም ክራይተርያ መሰረት ያደረገ /Criterion Referenced/ የነጥብ አሰጣጥ ስርአት መከተል። ለአፈፃፀምም ይረዳ ዘንድ አስፈላጊ የአፈፃፀም መመርያዎችን ማዘጋጀት፤ መግባባት መድረስ፤ ማስፈፀምና አፈፃፀሙን መከታተል | የተከታታይ ምዘናና ቋሚ መስፈርት መሰረት ያደረገ የነጥብ አሰጣጥ ስርአት እየተተገበረ እና ክትትል እየተደረገበት ነው። መጀመርያ አከባቢ የነበሩ ብዥታዎች በአሰራር ተደግፈው እየተቀረፉ ሲሆን ተጨማሪ ጥረቶች ግን የሚጠይቁ ናቸው። (አፈፃፀም 90%) | | |
| | 4.3 የደከሙ ተማሪዎችን በመለየት በተለይም ደግሞ የሴት ተማሪዎችን መሰረት ያደረጉ የቱቶርያልና | የቱቶርያል ድጋፍ በየኮሌጁና ትምህርት ክፍሉ የሚሰጡ ሲሆን ቱቶርያል በተመለከተ በአንደኛ ሰሚስተር የነበረው አፈፃፀም ደካማ ስለነበረ | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ረሜድያል ስራዎችን ማከናወን | በሁለተኛው ሰሚስተር እንዲሻሻል ተደርጓል። የአንደኛ ሰሚስተር ውጤታቸው አነስተኛ የሆኑ ተማሪዎች ተለይተው የረሜድያል ድጋፍ ተደርጎላቸው እንደገና እንዲፈተኑ ተደርጓል። (አፈፃፀም 80% | | |
